# በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
## የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ

# የ1998 በጀት ዓመት
# ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርት

ሐምሌ 1998

አዲስ አበባ

# በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

## የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ

# የ1998 በጀት ዓመት

# ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርት

ሐምሌ 1998

አዲስ አበባ

# ማውጫ

አርዕስት ገጽ


1. መግቢያ ........ 1
2. የኢኮኖሚክ ስታቲስቲክስ ........ 3
   - 2.1 የተፈጥሮ ሃብትና ግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት ........ 3
   - 2.2 የቤተሰብ በጀትና ዋጋዎች ስታቲስቲክስ ጥናት ........ 8
   - 2.3 የኢንዱስትሪ፣ንግድ፣ ትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ ጥናት ........ 13
3. የሥነ - ሕዝብ ስታቲስቲክስ ........ 16
   - 3.1 የማህበራዊ ስታቲስቲክስ ጥናት ........ 16
   - 3.2 የሕዝብና ቤት ቆጠራ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ........ 19
4. የ1998 በጀት ዓመት የፊዚካል ሥራ አፈጻጸም ........ 27
5. ሳምፐሊንግ ሜቶዶሎጂን በተመለከተ ........ 28
6. መረጃ ማቀነባበርን በተመለከተ ........ 31
7. የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ........ 33
8. የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ጽ/ቤት ዝግጅትን በተመለከተ ........ 35
9. የማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት ........ 39
10. የኦዲት አገልግሎት ........ 41
11. የሕግ አገልግሎት ........ 41
12. የፕላንና ፕሮግራም አገልግሎት ........ 42
13. የአስተዳደርና ፋይናንስ አገልግሎት ........ 43
   - 13.1 የሰው ኃይል ሁኔታ ........ 43
   - 13.2 የበጀት አጠቃቀም ........ 44
   - 13.3 አገልግሎት ነክ የሆኑ ጉዳዮች ........ 48
14. በዕቅድ አፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች ........ 51

# የ1998 ዓ.ም በጀት ዓመት
# የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት

## 1. መግቢያ

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በየጊዜው አዳዲስ የመረጃ አሰባሰብ ስልቶችን በመጠቀም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የስነ-ህዝብ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማቀነባበር፣ በመተንተንና በሪፖርት በማውጣት ለተጠቃሚዎች በማሰራጨት ላይ ይገኛል፡፡ እነዚህ መረጃዎች እንደተገልጋዩ ፍላጐት ለዕቅድ ወይም ለምርምር እንደዚሁም ለሌሎች ሥራዎች መነሻ በመሆን ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያበረከቱ ሲሆን፣ በ1998 በጀት ዓመትም መ/ቤቱ የመረጃ ተጠቃሚዎችን ፍላጐት፣ የመ/ቤቱን የማስፈፀም አቅምና የተመደበለትን በጀት ግምት ውስጥ በማስገባት የተለያዩ ጥናቶችን አቅዶ በርካታ ተግባራትን አከናውኗል፡፡

በዚህም መሰረት የመረጃ መሰብሰቡ ተግባር በ1997 ዓ.ም ተጀምሮ የመረጃ ማቀነባበሩ ተግባር ወደ 1998 የተሸጋገሩ የበልግ ወቅት የግብርና ናሙና ጥናት፣ የሰፋፊና መካከለኛ የግልና የመንግስት እርሻዎች ጥናት፣ የአትክልት፣ ሥራ ሥርና የቋሚ ሰብሎች ጥናት፣ የ1996 የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንድስትሪ ጥናት፣ የሰው ኃይል ጥናት እንዲሁም በውጭ ዕርዳታ የሚከናወኑ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት፣ የቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጪ ጥናት፣ የኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ የባህሪ ቅኝት ጥናትና የሚከተሉትን አዳዲስ ጥናቶች በዕቅድ በመያዝ ሰፊ የሥራ እንቅስቃሴ አድርጓል፡፡
እነዚህም:-

ሀ. የተፈጥሮ ሃብትና የግብርና ስታቲስቲክስ

- የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት፣
- የሰብል ምርት ጥናት በመኸር ወቅት፣
- የሰፋፊ የግል፣ የመንግሥትና የድርጅት እርሻዎች ጥናት፣
- የሰብል ምርት ጥናት በበልግ ወቅት፣
- የቤት እንስሳት፣ የዶሮ ኃብትና ንብ የያዙ ቀፎዎች ጥናት፣

ለ. የኢንዱስትሪ ስታቲስቲክስ

- የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣
- ወቅታዊ የማማረቻ የንግድና የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጥናት፣
- የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች የምርት መጠንና የአምራቾች ዋጋ ጥናት፣
- የኮንስትራክሽን ጥናት፣
- የማዕድንና ቁፋሮ ጥናት፣
- የአነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣
- የውጪ ንግድ ስታቲስቲክስ መረጃ ማሰባሰብና ማጠናቀር፣
- የትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ መረጃ ማሰባሰብና ማጠናቀር፣

ሐ. የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ስታቲስቲክስ

- የግብርና ምርቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት፣
- የዕቃዎችና የአገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት፣
- የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክሶች ዝግጅት /በዋናው መ/ቤት/
- የዓለም አቀፍ የንፅፅር ፕሮግራም፣

መ. የማኅበራዊ ስታቲስቲክስ

- ተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናት፣ እና

ሠ. የቆጠራ ካርታ ሥራ ማካሄድ ናቸው፡፡

## 2. የኢኮኖሚ ስታቲስቲክስ

### 2.1 የተፈጥሮ ሃብትና የግብርና ስታቲስቲክስ

#### 2.1.1 የሰብል ምርት ትንበያ ጥናትን በተመለከተ

ይህ ጥናት በየዓመቱ ያለመቋረጥ የሚያከናወን ሲሆን፤ የጥናቱ ውጤትም በበጀት ዓመቱ ሁለተኛ ሩብ ዓመት መጀመሪያ ላይ ለተጠቃሚ መድረስ አለበት:: በመሆኑም የ1998 ዓ.ም የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት ሪፖርት በታቀደው መሠረት ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ ተደርጓል:: ከዚህ በተጨማሪ ጥናቱን በተመለከተ የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት ተከናውነዋል:: እነዚህም

- ከ1998 የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት ከመስክ የተሰበሰበ በሰብል የተሸፈኑና በሌላ የመሬት አጠቃቀም የተያዙ የመሬት ስፋት መረጃዎችን በዞን፣ በክልልና በሀገር አቀፍ ደረጃ አቀነባብሮ በማዘጋጀት ለየክልሉ የግብርናና የገጠር ልማት ቢሮዎችና የፋኦ የምግብ አቅርቦትና የሰብል ግምገማ ቡድን ለሚያካሄዱት የሰብል ምርት ግምገማ ሥራ በግብአትነት መጠቀም እንዲችሉ ተሰጥቷል::

- የ1998 የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት በኮምፒውተር በማቀነባበር ካለፉት ሁለት ዓመታት መረጃዎች ጋር በማነፃፀር ሪፖርቱ ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል::

- በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲና በክልል የግብርና ቢሮዎች አማካኝነት በየዓመቱ የሚወጡት የሰብል ምርት ትንበያ መረጃዎች መካከል ከፍተኛ ልዩነት ይኖራል:: ይህንን የመረጃ ልዩነት ችግር ለመቅረፍና የተጣጣመ መረጃ ለተጠቃሚዎች ለማቅረብ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መ/ቤት ሰብሳቢነት የየክልሉ የመስተዳድር፣ የግብርና ቢሮ ኃላፊዎች የማ.ስ.ኤ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ስብሰባዎችን በማካሄድ በተወሰነ ደረጃ መግባባት ላይ በመደረሱ፣ ችግሩን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ዕልባት ለመስጠት ቀጣይ ውይይትና ግምገማ ለማድረግ የቴክኒካል ኮሚቴ ተቋቁሟል:: በዚህም የኤጀንሲው ባለሙያዎች በቴክኒክ ኮሚቴው ስብሰባ ላይ በመሳተፍና ተከታታይ ስብሰባ በማድረግ ውጤቱንና የውሳኔ ሃሳብ ለStreering ኮሚቴ እንዲቀርብ ተደርጓል::

### 2.1.2 የእርሻ መሬት ስፋትና የምርት መጠን መረጃ በተመለከተ

የእርሻ መሬት ስፋትና የምርት መጠን መረጃ በመኸር ወቅት ከሚከናወኑት የሰብል ምርት ናሙና ጥናት ውስጥ አንዱ ሲሆን፤ የጥናቱ 6.49 በመቶው በ1997 ዓ.ም ተከናውኗል:: ቀሪውን 93.51 በመቶ ተግባር በ1998 በጀት ዓመት ለማከናወን በዕቅድ ተይዞ 85.50 በመቶው ተጠናቋል:: ይህም ከዕቅዱ 91.4 በመቶ ነው:: በተጨማሪም ከ1997 ዓ.ም የተሸጋገረው የእርሻ መሬት ስፋትና የምርት መጠን የመረጃ ማቀነባበር ተግባር ከተከናወነ በኋላ ሪፖርቱ ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል:: ዝርዝሩም በሠንጠረዥ አንድ ላይ ቀርቧል::

### 2.1.3 የመሬት አጠቃቀም

ለሰብል ምርት ናሙና ጥናት ሪፖርት ከሚዘጋጅላቸው ጥናቶች ውስጥ የመሬት አጠቃቀም ጥናት ይገኝበታል:: የዚህ ጥናት የዝግጅት ሥራ በከፊል በ1997 በጀት ዓመት ማለትም 6.49 በመቶው የተከናወነ ሲሆን፤ በ1998 በጀት ዓመት ቀሪውን 93.51 በመቶ ተግባር ለማከናወን ታቅዶ 85.50 በመቶው ተጠናቋል:: በአሁኑ ሰዓት የጥናቱ ውጤት እየተገመገመ ሲሆን፤ ቀሪው ሪፖርቱን አትሞ ለተጠቃሚዎች የማቅረብ ሥራ በቅርብ ይጠናቀቃል::

በተመሣሣይ ከ1997 በጀት ዓመት የተሸጋገረው የመሬት አጠቃቀም ጥናት የመረጃ ማቀነባበር ተግባር ተከናውኖ የጥናቱ ሪፖርት ታትሞ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል::

### 2.1.4 የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታን በተመለከተ

በ1997 ዓ.ም የመኸር ወቅት የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ ጥናት ውጤት በበጀት ዓመቱ ተጠናቆ ስታቲስቲካል ሪፖርቱ ታትሞ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ የተደረገ ሲሆን፤ ይኸው ጥናት በ1998 ዓ.ም በተመሣሣይ ሁኔታ የመረጃ መሰብሰብ ሥራ ተጠናቆና ተቀነባብሮ የመረጃው ውጤት አስተማማኝነት እየተመረመረ ይገኛል:: ይህ ጥናት በበጀት ዓመቱ ይጠናቀቃል ተብሎ የታቀደ ሲሆን፤ የጥናቱ 91.4 በመቶ ተጠናቋል::

### 2.1.5 የቤት እንስሳት የዶሮ ሃብትና ንብ የያዙ ቀፎዎችን በተመለከተ

የ1998 ዓ.ም የቤት እንስሳት፣ዶሮ ሃብትና ንብ የያዙ ቀፎዎች ጥናትን ለማካሄድ የሚረዱ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ከ1997 ግንቦት ወር ጀምሮ የተካሄዱ ሲሆን፤ በበጀት ዓመቱ መረጃው ከመስክ ተሰብስቦ፣ ተቀነባብሮና ታትሞ በወቅቱ ለመረጃ ተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል:: ይህም በበጀት ዓመቱ ይሠራል ተብሎ የታቀደው 93.51 በመቶ ተግባር ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል::

### 2.1.6 የሰፋፊና የመካከለኛ ንግድ እርሻዎች መረጃን በተመለከተ

በ1997 ዓ.ም የመረጃ መሰብሰቡ ተግባር የተጠናቀቀለት የሰፋፊና የመካከለኛ እርሻዎች ጥናት ቀሪ ተግባር ማለትም ከአጠቃላይ ሥራው 35 በመቶ ወደ 1998 ዓ.ም የተሸጋገረ ሲሆን፤በበጀት ዓመቱ የመረጃ ማቀነባበር ሥራው ተጠናቋል:: ሆኖም የጥናቱ ውጤት አስተማማኝ ባለመሆኑ የሪፖርት ዝግጅቱ ተቋርጧል:: ይህም በበጀት ዓመቱ ከታቀደው (ከቀሪው የሥራ እንቅስቃሴ) የተከናወነው 71 በመቶ ነው::

በ1998 ዓ.ም የሚካሄደው የሰፋፊና የመካከለኛ እርሻዎች ጥናት በአገሪቱ እየተስፋፋ የሚገኘውን የአበባ እርሻ እንዲያካትት ለማድረግ መጠይቅ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል:: በበጀት ዓመቱ በዚህ ጥናት ለመስራት ከታቀደው 93.51 በመቶ ውስጥ 66 በመቶው ወይም ከታቀደው 70 በመቶ ሊጠናቀቅ ችሏል::

### 2.1.7 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት

በ1998 በጀት ዓመት ለሚከናወኑ ጥናቶች እንዲሁም የመረጃ መሰብሰብ ተግባራቸው በ1997 ዓ.ም የተጠናቀቀላቸው የዘርፉ ጥናቶችን ለማከናወን የሚረዱ የተለያዩ ሥራዎች እንዲሁም ሌሎች ለግብርና ስታቲስቲክስ የሚጠቅሙ ተግባራትን በተመለከተ የተከናወኑ ዋና ዋና ሥራዎች ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርበዋል::

- ለ1998 ዓ.ም ለቅድመ ማስጠንቀቂያ፣ ለመኸር፣ ለበልግ ወቅትና ለቋሚ ሰብል ምርት ትንበያና ለግብርና ናሙና ጥናት ከመስክ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችሉ አስፈላጊ የሆኑ ማሻሻያዎችንና አዳዲስ ቅጾችን ያካተቱ መጠይቆችና መመሪያዎች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ ውለዋል::

- ለ1998 ዓ.ም የቅድመ ማስጠንቀቂያ፣ የሰብል ምርት ትንበያ፣ ለዋናው መኸር ግብርና ናሙና ጥናት፣ ለቤት እንስሳት ጥናት ለበልግ ወቅት ጥናት ለሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎችን ጥናት በሚመለከት ከዋናው መ/ቤትና ከ25 ቅ/ጽ/ቤቶች ለተውጣጡ ባለሙያዎች የአሠልጣኞች ሥልጠና ከነሐሴ አጋማሽ ጀምሮ ለ20 ቀናት በ25ቱም ቅ/ጽ/ቤቶች ለመረጃ ሰብሳቢዎችና ለመስክ ተቆጣጣሪዎች ስልጠና ተሰጥቷል::

- በ1998 ዓ.ም ለሚካሄደው የምግብ ዋስትና ጥናት ማዘጋጃ የሚያገለግሉ Tabulation Plan ዝግጅት የተጠናቀቀ ሲሆን፣ የኤዲቲንግ ኮዲንግ መመሪያና የኮምፒውተር ኤዲት ስፔስፊኬሽን ዝግጅት ሥራ ተጠናቆ ለሚመለከተው ክፍል ተላልፎ ሥራ ላይ የዋለ ሲሆን፣ የመረጃው ቅንብር እየተገመገመ ይገኛል::

- መ/ቤቱ በየዓመቱ ለሚያዘጋጀው የስታቲስቲክስ መጽሔት የግብርናውን ዘርፍ የሚመለከቱ መረጃዎች ከሌሎች መ/ቤቶች በማሰባሰብና በመምሪያው የሚገኙትንም የማጠናቀር ሥራ ተጠናቆ ለሚመለከታቸው ተላልፏል::

- የ1997 ዓ.ም የቋሚ ሰብል፣ አትክልትና ሥራ ሥር ተክሎች ልዩ ጥናት መረጃ የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግና ቬሪፊኬሽን ሥራ እንዲሁም የዳታ ኢንትሪና የመረጃ ቅንብሩ ሥራ ተጠናቆ ሪፖርቱ ታትሞ ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል::

- ከ10 የቆጠራ ቦታዎች ላይ ከሚሰበሰብ የታረሰ መሬት ስፋት መረጃ ግብዓትነት በሳተላይት ለሚደረገው ግምገማ መረጃዎች ከሁሉም የቆጠራ ቦታዎች ተሰብስቦ የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግና ቬሪፊኬሽን ሥራና እንዲሁም ክሊኒንግና የቅንብሩ ሥራ ተጠናቆ ውጤቱ በECA የስብሰባ አዳራሽ

በተዘጋጀው workshop ጉዳዩ ለሚመለከታቸው በአገር ውስጥና በውጭ አገር ለሚገኙ ድርጅቶች ባለሙያዎች ቀርቧል::

- ለዋናው መኸር ጥናት ኤዲቲንግ ኮዲንግና ቬሪፊኬሽን የሚያገለግሉ መመሪያዎች፣ ኤዲት ስፔሲፊኬሽንና Tabulation Plan ዝግጅት ተጠናቆ ለሚመለከተው ተሰጥቷል::

- በግብርና ቆጠራ መረጃ ላይ መሠረት ያደረገ ለኢትዮጵያ ግብርና አትላስ ዝግጅት የሚያገለግል የትርጉም ሥራ ተካሄዷል::

- የግብርና ስታቲስቲክስን የሚመለከት ከሃገር ውስጥና ከውጭ አገር ለሚቀርቡ የመረጃ ተጠቃሚዎች ጥያቄ መልስ ተሰጥቷል::

- የኤጀንሲው መ/ቤት ከዓለም ባንክ ጋር በመተባበር ለሚያካሄደው Rural Investement Climate Survey በመ/ቤቱ በተቋቋመ ግብረሃይል በመሳተፍ የመጠይቅና የመመሪያ ዝግጅት ተጠናቆ ለህትመት ክፍል እንዲላክ ተደርጓል::

- በ1999 ዓ.ም ለሚካሄደው የሰብል ምርት ትንበያ ጥናትና የግብርና ናሙና ጥናት እንዲሁም ለሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች ጥናት የሚያገለግሉ መጠይቆችና መመሪያዎች ተዘጋጅተው የህትመቱ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል::

- በ1998 ከመስከረም እስከ ጥቅምት ወር በተካሄደው የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት የመረጃ ማሰባሰብ ሥራ የመ/ቤቱ ባለሙያዎች በመስክ በመገኘት ሥራውን በመገምገምና ሙያዊ ዕገዛ በማድረግ ለመረጃው ጥራት ከፍተኛ አስተዋኦ አድርገዋል:: በተጨማሪም በኅዳር 1998 ለአንድ ወር ያህል ከFAO Crop Assesment Mission ጋር በመሆን በሰብል ምርት ግምገማ ጥናት ላይ ተሳትፎ ተደርጓል::

## 2.2 የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ስታቲስቲክስ

### 2.2.1 የዋጋዎች ጥናትና የዋጋ ኢንዴክስን በተመለከተ

**ሀ. በገጠር የግብርና ውጤቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት**

- የአምራቾች ዋጋ ጥናት የመረጃ አሰባሰብ መመሪያ በማዘጋጀት ለመረጃ ሰብሳቢዎችና ለመስክ ተቆጣጣሪዎች ስልጠና የተሰጠ ሲሆን፣ ለዕቅድ ዓመቱ የሚያገለግል መጠይቅም ታትሞ ለቅ/ጽ/ቤቶች እንዲሠራጭ ተደርጓል::

- ከሐምሌ ወር 1997 እስከ መጋቢት ወር 1998 ዓ.ም ያለው የአምራቾች ዋጋ ጥናት ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል:: እንዲሁም የሚያዝያ ወር መረጃ ተዘጋጅቶ ለህትመት የተላከ ሲሆን፣ የግንቦትና የሰኔ ወር 1998 መረጃ በመቀነባበር ላይ ይገኛል:: ይህም ከታቀደው 97 በመቶ ውስጥ 93 በመቶው እንደተጠናቀቀ ያሣያል::

**ለ. ወርሃዊ የዕቃዎችና የአገልግሎቶች ዋጋ ጥናት**

- ለጥናቱ የመረጃ አሰባሰብ መመሪያን በማዘጋጀት ለመረጃ ሰብሳቢዎችና ተቆጣጣሪዎች ስልጠና በመስጠት የመረጃ መሰብሰብ ተግባር ተጠናቋል:: እንዲሁም ለዕቅድ ዓመቱ የሚያገለግል መጠይቅ ተባዝቶ ለቅ/ጽ/ቤቶች ተሰራጭቷል::

- ከሐምሌ 1997 ዓ.ም እስከ ሚያዝያ ወር 1998 ዓ.ም ያለው ሪፖርቱ ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል:: እንዲሁም የግንቦት ወር 1998 መረጃ ተቀነባብሮ ለህትመት የተላከ ሲሆን፣ የሰኔ ወር 1998 መረጃ በመቀነባበር ላይ ይገኛል:: ይህም ከታቀደው 97 በመቶ ውስጥ 95 በመቶ እንደሆነ ያመለክታል::

ሐ. ወርሃዊ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አሃዝ

- የሃገር አቀፍና የክልሎች

  - የሀገር አቀፍና የክልሎች የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አሃዝ ከሐምሌ ወር 1997 ዓ.ም እስከ የካቲት 1998 ዓ.ም ድረስ ያለው መረጃ በየወሩ ታትሞ ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ ተደርጓል::
  - የሰኔ ወር 1998 ዓ.ም አሃዝ በመቀነባበር ላይ ይገኛል::

- የሸማቶች ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስን በአዲስ መልክ ማዘጋጀት

በ1996/97 ዓ.ም የተከናወነውን የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት መሠረት ያደረገ የሸማቶች ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ በአዲስ መልክ Consumer Price Index (IPT) ለማዘጋጀት የተለያዩ የቅድመ ዝግጅቶች ተከናውነዋል:: እነዚህም

- ከመረጃ ተጠቃሚዎች ጋር የግማሽ ቀን ውይይት ተደርጓል፣
- የተለያዩ የጽሑፍ አስተያየቶች ተሰብስበዋል፣
- የዓለም የገንዘብ ድርጅት ለባለሙያዎች የ12 ቀናት ስልጠና ተሰጥቷል፣ እንዲሁም
- የ1996/97 ዓ.ም ተከናወነውን የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት መሰረት ያደረገ ጥናት በአዲስ አበባና በኦሮሚያ ክልል ተከናውኗል::

- የአዲስ አበባ ከተማ

  - የአዲስ አበባ ከተማ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አሃዝ ከሐምሌ ወር 1997 ዓ.ም እስከ ሰኔ 1998 ዓ.ም ድረስ ያለው መረጃ በየወሩ እየተቀነባበረና እየታተመ ለተጠቃሚዎች በወቅቱ ተሰራጭቷል::

መ. የዓለም አቀፍ ንጽጽር መርሃ -ግብር በአፍሪካ

ይህ ጥናት የአፍሪካ ሃገሮችን ገንዘብ የመግዛት አቅም ለማስላት የሚያስችል ጥናት ሲሆን፤ ከአፍሪካ ልማት ባንክ እና ከምሥራቅና ደቡብ አፍሪካ

የንግድ ቀጠና (COMESA) ጋር በመተባበር በመ/ቤቱ የሚካሄድ ነው:: በመሆኑም በበጀት ዓመቱ የሚከተሉት ተግባራት ተከናውነዋል::

- <u>የቅድመ ዝግጅት ሥራን በሚመለከት</u>

  - ለጥናቱ የሚያስፈልጉ ዶኩመንቶችን የማሰባሰብ፣ የድርጅቶች መመዝገቢያ ቅጾችን፣ የመረጃ ማሰባሰቢያ መጠይቆችንና መመሪያዎችን የማሻሻልና የእርምት ሥራ ተከናውኗል:: የድርጅቶች መመዝገቢያ ቅጽ የመረጃ አሰባሰብ መመሪያና ለ12 ወራት መረጃዎችን ለማሰባሰብ የሚያስችል መጠይቆች እንዲባዙ ተደርጓል::

  - ለቅ/ጽ/ቤቶች የመስክ ሠራተኞችና ባለሙያዎች በዋናው መ/ቤት ከታህሳስ 10-17/1998 ዓ.ም ድረስ ሥልጠና ተሰጥቷል:: ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ለማግኘት በሀገር ውስጥ ለሚገኙ ተቋማትና በውጭ ለሚገኙ ከአፍሪካ ልማት ባንክና ከምሥራቅና ደቡብ አፍሪካ የንግድ ቀጠና (COMESA) ባለሙያዎች ጋር ደብዳቤ የመፃፍ ሥራ የተከናወነ ሲሆን፤ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች ግዥ በመካሄድ ላይ ይገኛል:: ጥናቱን ለማስተዋወቅ የሚያችል ጽሁፍ በማዘጋጀት የመገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም መግለጫ ተሰጥቷል::

- <u>መረጃ የማሰባሰብና የማቀነባበር ተግባራትን በሚመለከት</u>

  - በአገር አቀፍ ደረጃ ለICP መረጃ መሰብሰብ የሚያስችሉ በደንበኝነት ለሚያዙ ድርጅቶች ምዝገባና መረጣ ከታህሳስ 20 -23/1998 ባለው ጊዜ ተካሄዷል::

  - የዚህ ጥናት መረጃ የማሰባሰቡ ተግባር ከሐምሌ 1997 እስከ ታህሣስ 1998 ዓ.ም ድረስ በአዲስ አበባ እንዲሁም ከጥር 1998 እስከ መጋቢት 1998 ድረስ በሁሉም ክልሎች ተጠናቋል::

  - የዚህ ጥናት መረጃ በኮምፒውተር የማረምና የማስተካከል የመጨረሻ የሚሆነው የተሰበሰበው መረጃ ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች መረጃ ጋር ተወዳድሮ አጥጋቢ ሲሆን ብቻ ነው:: በመሆኑም ከሐምሌ ወር 1997 እስከ ሚያዝያ ወር 1998 ዓ.ም ድረስ ያለው መረጃ ከ (COMESA) አገሮች መረጃ

እንዲሁም ከሁሉም አገሮች መረጃ ጋር ተወዳድሮ መጠነኛ አለመጣጣም ለታየባቸው መረጃዎች በድጋሚ ማስተካከያ ተደርጐ ወደ አፍሪካ ልማት ባንክ ተልኳል::

- የግንቦትና የሰኔ ወር 1998 የዓለም አቀፍ ንጽጽር መርሃ ግብር መረጃ የዳታ ኤዲቲንግ ኮዲንግና ኢንትሪ ሥራ ተካሄዶ የመረጃ ማቀነባበሩ ሥራ በመካሄድ ላይ ይገኛል:: የአዲስ አበባ ከተማ ከሐምሌ 1997 እስከ ታህሳስ 1998 በሃገር ደረጃ የማረሙ ሥራ ተካሄዶ ወደ አፍሪካ ልማት ባንክ የተላከ ሲሆን ከሌሎች አገሮች መረጃዎች ጋር ተወዳድሮ ልዩነት ለታየባቸው ተጨማሪ የማረምና የማስተካከል ሥራ ተከናውኗል::

- በICP Africa ዋጋ ጥናት መረጃ ላይ በመረጃ እርማት ወቅት የታዩ ችግሮችን በመሰብሰብና ተጨማሪ መመሪያም በማዘጋጀት ከመስክ ሠራተኞች ጋር ውይይት በማድረግና ዶኩመንት በመስጠት ግድፈቶች በቀጣይ ሥራ ወቅት እንዳይደገሙ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል::

- የዚህ ጥናት አካል የሆነው የመድሃኒት ዋጋ መረጃ የታህሳስ፣ የየካቲትና የግንቦት ወር ተሰባስቦና የእርማት ሥራ ተሠርቶ ለአፍሪካ ልማት ባንክ ተልኳል::

- የነዳጅ ዋጋ ንረት በኢኮኖሚው ላይ ያለውን ተፅዕኖ በሚመለከት መረጃ የማሰባሰብ ተግባር ከህዳር 5 እስከ ታህሳስ 5 ቀን 1998 ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ ትላልቅ የነዳጅ ማደያ ድርጅቶች ተካሄዶ፣ መረጃው ኮምፒውተር ተቀነባብሮ ለአፍሪካ ልማት ባንክ ተልኳል::

- የገበያ መረጃ ስርዓትን በሚመለከት ከምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ቢሮ በቀረበ ጥያቄ መሠረት ለጥናቱ የሚሆን ፕሮጀክት የተዘጋጀ ሲሆን፣ በጀቱ ሲፀድቅ ለክልል የምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ቢሮዎች በመላክ በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በትግራይና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልሎች በተመረጡ 144 የመገበያያ ቦታዎች መረጃውን በየሳምንቱ የመሰብሰብ ሥራ ይከናወናል::

### 2.2.2 የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናትን በተመለከተ

የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት በቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና በተለያዩ ወጪዎች ላይ በማተኮር ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን በመሰብሰብ በአገሪቱ የተንሰራፋውን የድህነት ሁኔታ፣ ስርጭት፣ ስፋትና ጥልቀት ለመገምገምና ለመከታተል የሚያስችል መረጃ የሚያስገኝ ነው።

ጥናቱ የድህነትን ገፅታ ከቤተሰቦች ገቢ አንፃር የሚያመለክት (Income Dimension of poverty) ሲሆን፣ የድህነት ወለልን ለመወሰን የሚያስችል መረጃ የሚያስገኝ ነው። ጥናቱ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ለመንደፍ፣ ትግበራውን ለመከታተልና ለውጦችን ለመገምገም ብሎም የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦችን ለመከታተል የሚያስችል መረጃ የሚመነጭበት ነው።

በመሆኑም በ1996/97 በሁለት ዙር የመረጃ መሰብሰብ ተግባር የተጠናቀቀለት የቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጪ ጥናት በአሁኑ ጊዜ መረጃዎችን የመገምገም ሂደት እየተከናወነ ይገኛል። ይህም ጥናቱ የተካሄደው በሁለት ዙሮችና እያንዳንዱን ቤተሰብ ለአሥራ ስድስት ጊዜ እየተመላለሱ መረጃ በመሰብሰብ ሲሆን፤ የጥናቱ ባህሪ ሰፊ ጊዜ የሚፈልግ በመሆኑ የሪፖርቱ ሥራ እስከአሁን አልተጠናቀቀም።

### 2.2.3 የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት በተመለከተ

በ1996 በጀት ዓመት የመረጃ መሰብሰብ ተግባር የተጠናቀቀለት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት የመረጃ ማቀነባበርና የሪፖርት ዝግጅቱ ተጠናቆና ታትሞ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

### 2.2.4 ልዩ ልዩ ሥራዎች

- በእንግሊዘኛ ተዘጋጅቶ የነበረውን የ5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የክትትል የግምገማ ስርዓት ሰነድ ወደ አማርኛ እንዲተረጎም ተደርጓል።

- መ/ቤቱ ለሚያዘጋጀው ዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት የሚያገለግሉ ዘርፉን የሚመለከቱ መረጃዎች ከልዩ ልዩ መ/ቤቶች ተሰባስበውና ተቀነባብረው ለሚመለከተው አካል ተሰጥተዋል::

- የኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ጥናትን በሚመለከት ለጥናቱ የተዘጋጀውን የእንግሊዝኛ መጠይቅ ወደአማርኛ የመተርጐም ሥራ ከመከናወኑም ባሻገር ለጥናቱ የሚያስፈልጉ የመረጃ ማሰባሰቢያ መጠይቆችና የመረጃ አሞላል መመሪያም ተዘጋጅቶ ለመስክ ሥራ ሠራተኞች ሥልጠና ተሰጥቷል::

- በሌላ በኩል የ1999 የገጠር ኢንቨስትመንት ጥናትን በሚመለከት እስካሁን ድረስ የተዘጋጀውን መጠይቅ ወደ አማርኛ የመተርጐም ሥራ ተከናውኗል:: እንዲሁም የመረጃ አሰባሰብ መመሪያ የማዘጋጀቱ ሥራ ተጀምሯል::

## 2.3 <u>የኢንዱስትሪ፣ ንግድ ትራንስፖርት መገናኛ ስታቲስቲክስ</u>

### 2.3.1 <u>የኢንዱስትሪ ስታቲስቲክስ ጥናቶች በተመለከተ</u>

### ሀ. <u>የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት</u>

- በ1997 የዕቅድ ዘመን የመረጃ ማሰባሰቡ ተግባር የተጠናቀቀለት የ1996 በጀት ዓመትን የሚመለከተው የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ ሪፖርቱ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል::

- ከጀንዋሪ 2005 እስከ ዲስምበር 2005 ድረስ ያለው የManufacturing የአምራቾች ዋጋ ተሰብስቦ፣ ተጠናቅሮ፣ ኢንዴክሱ ተሰልቶና ተተንትኖ መረጃ ተጠቃሚዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች ተልኳል::

- የ1997 የአራተኛ ሩብ ዓመት የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናትና የ1998 የመጀመሪያ፣ የሁለተኛና ሦስተኛ ሩብ ዓመት ወቅታዊ ጥናት ከመረጃ መሰብሰብ እስከ ሪፖርት ዝግጅት ድረስ ያለው ሥራ ተከናውኖ ሪፖርቱ

ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል፡፡ ይህም በዕቅድ የተያዘው ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል፡፡

- በ1998 ዓ.ም የመረጃ መሰብሰቡ ተግባር ለሚካሄድለት የ1997 ዓ.ም የትላልቅና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ጥናት የመጠይቅና መመሪያ ዝግጅት ተጠናቆ ለመረጃ ሰብሳቢዎች፣ ተቆጣጣሪዎችና ስታቲስቲሽያኖች ስልጠና በመስጠት የመረጃ መሰብሰቡ ተግባር ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል፡፡ ይህም በዕቅድ ከተያዘው 60 በመቶ ውስጥ 60 በመቶ ማለትም 100% ተጠናቋል፡፡ ቀሪው ሥራ ወደ 1999 ዓ.ም ተሸጋግሮ ሪፖርቱ በሚቀጥለው ዓመት ለተጠቃሚዎች ይደርሣል፡፡

ለ. <u>የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት</u>

ለአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት የመጠይቅና የማንዋል ዝግጅት ሥራ ተከናውኖ ለመረጃ ሰብሳቢዎችና ለተቆጣጣሪዎች እንዲሁም ለስታቲስቲሽያኖች ሥልጠና ተሰጥቶና የመረጃ ማሰባሰቡ ተግባር ተጠናቆ በቢሮ ደረጃ የዳታ ኢንትሪ ሥራው በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ ይህም በዕቅድ ከተያዘው አጠቃላይ ሥራ 75 በመቶው የተጠናቀቀ ሲሆን፤ የጥናቱ ሥራ ሙሉ በሙሉ ያልተጠናቀቀው በመረጃ ማቀነባበር ተግባር ላይ የብዙ ጥናቶች መደራረብ በመኖሩ ነው፡፡

ሐ. <u>የኢኮኖሚ ድርጅቶች ቆጠራ</u>

በ1995 ዓ.ም ጥናቱ ለተካሄደለት የአኮኖሚ ድርጅቶች ቆጠራ መረጃን ጥራት ለማሻሻልና ዳታ ቤዝ ለመፍጠር ከዓለም ባንክ ከተላኩ አማካሪ ጋር በመሆን በርካታ ሥራዎች ተከናውኗል፡፡

መ. <u>የኮንስትራክሽን ጥናት</u>

በ1998 ዓ.ም ሊካሄድ የነበረው የኮንስትራክሽን ጥናት አዲስ ሥራ በመሆኑ ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ የዓመቱን ጥናት በሙከራ ደረጃ እንዲካሄድ መ/ቤቱ በመወሰኑ የሙከራ ጥናት ተካሄዶ ውጤቱ እየተገመገመ ይገኛል፡፡

## ሠ. የንግድ፣ ትራንስፖርትና መገናኛ መጽሔትን በተመለከተ

- ለትራንስፖርትና መገናኛ መጽሔት የሚሆኑ መረጃዎች ከየመ/ቤቶች የመሰብሰብ ሥራ ተጠናቆ የመጽሔት ዝግጅቱ ሥራ የተካሄደ ቢሆንም የትራንስፖርት መረጃ በዋነኛነት የሚገኘው ከመንገድ ትራንስፖርት በመሆኑ በቂ መረጃ ከዚህ ዘርፍ ለማግኘት ሙከራ ቢደረግም የተገኘው መረጃ አጥጋቢ ስላልሆነ የመረጃውን ሪፖርት ለተጠቃሚዎች ለማድረስ አልተቻለም::

- የዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት የትራንስፖርትና መገናኛ መረጃዎች የመሰብሰብ ተግባር ተከናውኖ ለሚመለከተው ተላልፏል::

- የኢንፎርሜሽንና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ አመልካች ላይ ጥናት ለማካሄድ የቅድመ ዝግጅት ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል::

- የውጭ ንግድ መረጃን ለጠየቁ ተጠቃሚዎች አስፈላጊው መረጃ ተሰጥቷል::

## ረ. የማዕድንና ቁፋሮ ጥናት

በበጀት ዓመቱ ለሚካሄደው የማዕድንና ቁፋሮ ጥናት የመጠይቅ፣ የመመሪያና የፍሬም ዝግጅት ተጠናቆ፣ የተጠናቀቀ ቢሆንም መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ፍሬም ባለመገኘቱ ምክንያት ጥናቱ ሙሉ በሙሉ ሣይከናወን ቀርቷል::

## ረ. ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎች

በዚህ ዓመት ለሚካሄዱ ጥናቶች በፍሬምነት የሚያገለግሉ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፣ የግንባታ ሥራ ተቋራጮች፣ በድንጋይ አሸዋና ሌሎች ማዕድናትን በማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች ዝርዝር የማውጣት ሥራ ተከናውኗል::

# 3. የሥነ-ሕዝብና የማኅበዊ ስታቲስቲክስን በተመለከተ

## 3.1 የማህበራዊ ስታቲስቲክስን በተመለከተ

### 3.1.1 የሰው ኃይል ስታቲስቲክስ

በ1997 ዓ.ም የመረጃ ማሰባሰቡ ተግባር የተጠናቀቀለት የሰው ኃይል ጥናትን በሚመለከት የተሰበሰበው መረጃ የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግና የመረጃ ማቀነባበር ተግባር ተካሄዶ ሪፖርቱ ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል:: ይህም በበጀት ዓመቱ ሊከናወን የታቀደው 35 በመቶ ዕቅድ ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል:: እንዲሁም የጥናቱን ውጤት በክልል ደረጃ ለማዘጋጀት ከጥናቱ ውስጥ ተስማሚ የሆኑትን አመልካች (Indicators) የመምረጥ ሥራ በመካሄድ ላይ ይገኛል::

### 3.1.2 ተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናትን በተመለከተ

- በ1998 ዓ.ም ለሚካሄደው ተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናት ደጋፊ የሚሆኑ ዶክመንቶች የማሰባሰቡ ተግባር የተከናወነ ሲሆን፣ የሥራ መርሃ ግብር፣ የመረጃ ማሰባሰቢያ መጠይቆች፣ የመረጃ ሰብሳቢና የተቆጣጣሪዎች መመሪያዎችና የድርጅት ዋና ምርት/አገልግሎት ምደባና መለያ ኮድ መጽሐፍ ተዘጋጅተው ሥራ ላይ ውለዋል::

- ከመስክ የመረጃ ማሰባሰቡ ተግባር የተጠናቀቀለት ተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናት የዳታ ኤዲቲንግ፣ ቬሪፊኬሽን፣ ዳታ ኢንትሪና የክሊኒንግ ሥራ ተጠናቆ የቅንብሩ ሥራ በመካሄድ ላይ ይገኛል:: በተጓዳኝ መረጃው እየተገመገመ የሪፖርቱ የመጀመሪያው ምዕራፍ በመከናወን ላይ ነው:: ይህም በበጀት ዓመቱና በሚቀጥለው ዓመት በሁለት ምዕራፍ ሊካሄድ የታቀደውን የመረጃ መሰብሰብ ተግባር በአንድ በማጠቃለልና አንድ ሪፖርት ለማውጣት በማቀድ የሥራውን 80 በመቶ ለማከናወን ተችሏል::

### 3.1.3 የትምህርት ባህልና ስፖርት ስታቲስቲክስን በተመለከተ

- ለ1997 ዓ.ም ዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት የሚያስፈልጉ የትምህርት፣ የባህልና ስፖርት፣ የጤና፣ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችሉ መጠይቆችና ቅጾች ለሚመለከታቸው የክልልና የፌዴራል

መ/ቤቶች ተልከው መረጃዎች ተሞልተው የተመለሱ ሲሆን፣ ለተጠቃሚዎች በሚያመች ሁኔታ ተጠናቅረው ለሚመለከተው ክፍል ተላልፈዋል።

- በ1996 ዓ.ም ከክልል ተሞልተው የመጡ የትምህርት መጠይቆች ተፈትሸው የታዩ ጉድለቶች እንዲስተካከሉ ለማድረግ አንድ ጥራዝ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው የስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶች ተልኳል።

- ለዓመታዊ መጽሔት ዝግጅት መረጃዎች ከክልልና ከፌዴራል መ/ቤቶች ተሞልተው ሲመጡ ወደ ኮምፒውተር የሚገቡበትና የሚጠናቀሩበት እንዲሁም መጽሔቱ ታትሞ ሲወጣ ተጠቃሚዎችን የሚያረካ እንዲሆን የሚያስችል ሠንጠረዥ ተዘጋጅቷል።

- ለባህል ጥናት ዕገዛ ሊያደርግ የሚያስችል ዶኩመንትና መነሻ የሚሆን መጠይቅ ተዘጋጅቷል።

### 3.1.4 <u>የሕግና ደንብ ስታቲስቲክስ በተመለከተ</u>

- ለ1997 ዓመታዊ መጽሔት ዝግጅት የመረጃ ማሰባሰቢያ ቅጾች ለስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶችና በአዲስ አበባ ውስጥ ለሚገኙ ለሚመለከታቸው ለፌዴራልና ለክልል ቢሮዎች ተልከው መረጃዎች ተሞልተው ከመጡ በኋላ ወደ ኮምፒውተር በማስገባትና በማቀነባበር ለሚመለከተው እንዲደርስ ተደርጓል።

- ህግና ደንብን በሚመለከተ የአሠራር ሥርዓትን በማሻሻል የሥራ መርሃ ግብር ተዘጋጅቷል። እንዲሁም የህግና ደንብ የአሠራር ማሻሻያው ምዕራፍ ሰባትና ስምንት የሥራ መርሃ ግብር ዝግጅትና በህግና ደንብ ሥር መጠናት ለሚገባቸው የተለያዩ ጥናቶች በፍሬምነት የሚያገለግሉ መረጃዎች የሪፖርት ዝግጅት ሥራ ተጠናቋል።

- ከሁለተኛ ምንጭ የሚገኙ መረጃዎችን ይዘት ለማሻሻል ከመረጃ ሰጭ መ/ቤቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ሊገኙ የሚችሉ መረጃዎችን ለማጥናት የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት ተጠናቋል።

### 3.1.5 የጤናና አመጋገብ

- በ1997 ዓ.ም የመረጃ መሰብሰብ ተግባር የተከናወነለት የኤች አይ.ቪ/ ኤድስ የባህርይ ቅኝት ጥናት በበጀት ዓመቱ ለማከናን ከታቀደው 35 በመቶ ተግባር ውስጥ 25 በመቶው ወይም ከዕቅዱ 71 በመቶው ተከናውኗል::

- ቀደም ሲል የተዘጋጀውን የኤች. አይ. ቪ /ኤድስ የባህርይ ቅኝት ጥናት የኤዲቲንግና የኮዲንግ ማንዋል ግምገማ ተካሂዶ ለኤዲቲንግና ኮዲንግ ሠራተኞች ሥልጠና ተሰጥቷል::

- በባህርይ ቅኝት ጥናቱ በተካተቱ በአዲስ አበባ በሚገኙ 25 ት/ቤቶች ውስጥ የወንድና የሴት ተማሪዎች፣ የመምህራን፣ የቤተሰብ፣ የከባድ መኪናና የአገር አቋራጭ አውቶብስ ሾፌሮች፣ ከአርብቶ አደር፣ ከሴተኛ አዳሪ ሴቶችና፣ ከፖሊስ ሠራዊትና ከመከላከያ አባላት እንዲሁም ከፋብሪካ ሠራተኞች የተሰበሰበው መረጃ የኤዲቲንግና የቬሪፊኬሽንና የዳታ ኢንትሪና ክሊኒንግ ሥራ ተጠናቋል:: ከላይ ከተዘረዘሩት የህብረተሰብ ክፍሎች ጥናት መካከል የሴትና የወንድ ተማሪዎች ጥናት፣ የቤተሰብ፣ የከባድ መኪና ሹፌሮች የሆቴል ሠራተኞች ውጤትን በሚመለከት የኤዲት፣ ስፔስፊኬሽን የክሊኒንግና ሪፖርት ሠንጠረዦች ተጠናቀው ለመረጃ ማቀነባበሪያ ተሰጥቷል::

- በሌላ በኩል የወንድና ሴት ተማሪዎች፣ የመምህራን የቤተሰብ የከባድ መኪና ሹፌሮች የአውቶብስ ሹፌሮች የመንገድ ኮንስትራክሽን ሠራተኞች የመከላከያ የአርብቶ አደሮችና የፋብሪካ ሠራተኞችን የሚመለከተው የባህሪ ቅኝት ጥናት መጠይቅ የኮምፒውተር ፕሮግራም ሥራ ተጠናቆ የመረጃ ማስፈሪያ ሠንጠረዦች በመካሄድ ላይ ያለ ሲሆን፣ የቤተሰብ መጠይቅ ጥናት ውጤት የሪፖርት ሠንጠረዥ ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ የማጣራት ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል::

- በአዲስ አበባ ከተማ ሲኒማና ትያትር ቤቶች መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል መጠይቅና የአሞላል መመሪያ ተዘጋጅቶ ለየድርጅቶቹ የተላከ ሲሆን፣ የመ/ቤቱ ባለሙያዎች በየድርጅቶቹ በመዘዋወር መረጃ በትክክል እንዲሞላ

በማድረግ ሙያዊ እገዛ አድርገዋል:: በዚሁ መሠረት በአሁኑ ወቅት የአዲስ አበባ ከተማ ሲኒማና ቲያትር ቤቶች መረጃ የTabulation Plan ዝግጅት ተጠናቋል::

- በየዓመቱ ለሚዘጋጀው ስታቲስቲክስ መጽሔት የሥነ ሕዝብና የጤና መረጃዎች ተዘጋጅተው ለሚመለከተው ተሰጥተዋል::

- በዓለም ጤና ድርጅት በHealth Net Work Matrix አማካይነት ለመ/ቤቱ የሚሰጠውን የሥራ ዝርዝሮችና የገንዘብ መጠን የዕርዳታ ዓይነት ለመለየት እንዲቻል ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ባለሙያዎች ጋር በመተባበር ፕሮፖዛል ተዘጋጅቶ ተልኳል::

### 3.1.6 ሌሎች ሥራዎች

- ቀደም ሲል በተዘጋጀው የሥራ ውጤት ማሻሻያ (Business Process Enginering ) ዶኩመንት ላይ አስተያየት ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው ቀርቧል::

- ለተለያዩ መንግሥታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች የመረጃ መስጠትና ሙያዊ ዕገዛ የማድረግ ተግባር ተከናውኗል::

## 3.2 የሕዝብና ቤት ቆጠራ የቅድመ ቆጠራ ዝግጅት ሥራዎችን በተመለከተ

### 3.2.1 የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ

- በአገራችን ለሦስተኛ ጊዜ በ1999 ዓ.ም ለሚካሄደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር እንዲቻል አገሪቱን በቆጠራ ቦታዎች የመሸንሸኑ ሥራ ተጠናክሮ የተካሄደ ሲሆን፤ በበጀት ዓመቱ የ32,458 የቆጠራ ቦታ ካርታዎች ተሰርተዋል:: ይህም ከበጀት ዓመቱ እስከ ሦስተኛው ሩብ ዓመት ድረስ በመላው አገሪቱ በ92 የሥራ ቡድኖች የሸንሸና ሥራው ሊካሄድ የነበረ ሲሆን፤ ከመጋቢት ወር በኋላ ተጨማሪ 38 የሥራ ቡድኖች በመጨመር የካርታ ሥራው ተከናውኗል:: በመሆኑም ሥራው ከበጀት ዓመቱ ዕቅድ ጋር ሲነፃፀር 86 በመቶ ሲሆን፤ በአጠቃላይ ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ የተከናወነው ይሠራል ተብሎ ከሚጠበቀው ጋር ሲነፃፀር 76 በመቶው ተጠናቋል ቀሪው

በ1999 በጀት ዓመት ሁለተኛ ሩብ ዓመት ድረስ ይጠናቀቃል ተብሎ ታቅዷል:: ከዚህ በተጨማሪ የሚከተሉት ተግባራት ተከናውነዋል::

- ለቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ የሚያስፈልጉ የመነሻ ካርታዎች፣ የተለያዩ ቅጾችና የጽሕፈት መሣሪያዎችን በማደራጀት ወደ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንዲላኩ ተደርጓል::

- የቆጠራ ካርታ ዲጂታይዜሽን ሥራ ለማፋጠን እንዲቻል የካርታ ሥራ ኤጀንሲ ባለሙያዎች አግባብነት ካለው የሥራ ዘርፍ የኤጀንሲውን ሠራተኞች በመመልመልና በማስተባበር በዲጂታይዜሽን ካርታ ሥራ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል::

- ከመስክ ተጠናቀው የተላኩ የቤተሰብ ምዝገባና የኮርዲኔቶች ዝርዝር በተዘጋጀው የዳታ ኢንትሪ ፕሮግራም መሠረት በኮምፒውተር የመቅረጽ ተግባርና በጂ.አይ.ኤስ በመታገዝ የቆጠራውን ውጤት ለተጠቃሚ ለማቅረብ የተወሰኑ ወረዳዎች ካርታ ዲጂታይዝድ ተደርገዋል::

- የገጠርና የከተማ የቤተሰብ መመዝገቢያ ቅጾች፣ የድንበርና የውስጥ ገጽታዎች መመዝገቢያ ቅጽ እንዲሁም መረጃዎችን ኤዲትና ኮድ በማድረግ የ10 ወረዳዎች በኮምፒውተር የመቅረጽ ሥራዎችና ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎች ተከናውነዋል::

- የትምህርት ሁኔታን በተመለከተ ካለፈው ቆጠራ ወዲህ በሥራ ላይ የዋለውን አዲሱን የትምህርት ፖሊሲ፣ የትምህርት ደረጃዎች አከፋፈልና ዕውቅና የተሰጣቸው የግል ኮሌጆች ዝርዝር ከትምህርት ሚኒስቴር የተገኘ ሲሆን፤ ቤቶችን በተመለከተ ደግሞ ከአዲስ አበባ ከተማና ከኪራይ ቤቶች አስተዳደር በተገኘው መረጃ መሠረት የቆጠራ መጠይቅ ዝርዝርና አማራጭ መልሶቻቸው በቴክኒክ ኮሚቴው በኩል ተዘጋጅተው ለመ/ቤቱ ከፍተኛ ባለሙያዎች በማቅረብ አስተያየቶችንና ተጨማሪ ሃሳቦችን በማካተት በሥራ አመራር ተገምግሞ የመረጃ ፍላጎት የመወሰን ሥራ በመ/ቤቱ ደረጃ ተካሄዷል::

- የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን እንደገና ለማቋቋም፣ በወጣው አዋጅ አንቀጽ 7 ተራ ቁጥር 5 መሠረት ኮሚሽኑ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣትና የብሔረሰቦች ብዛትና ሥርጭትን ለማወቅ የሚያስችል በቆጠራ ወቅት የሚሰበሰበውን የብሔረሰቦች ዝርዝር ለማዘጋጀት እንዲቻል ከፌዴሬሽን ምክር ቤት ጋር በመተባበር ሥራውን እየተካሄደ ያለ ሲሆን፣ እስካሁን ድረስ ከ3 ክልሎች ማለትም ከትግራይ፣ ከአፋርና አማራ በስተቀር የሌሎች ክልሎች ዝርዝር ደርሷል።

- በ1999 ዓ.ም ለሚካሄደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ የአካል ጉዳተኞችን መረጃ ለመሰብሰብ መካተት የሚገባቸውን ጥያቄ የማካተትና ዶክመንቶቹን የመለየት እንዲሁም የሌሎች አገሮች ልምድን ግምት ውስጥ በማስገባት የመረጃ ማሰባሰቢያ ቅጾችን ለማዘጋጀት ተሞክሯል።

- የቆጠራውን የመጠይቅ አሞላል መመሪያ ዝግጅት፣ የጥያቄዎችንና መልሶችን ብዛትና ዓይነት ለመወሰንና ለማዘጋጀት በቆጠራው የሚሰበሰበውን የመረጃ ፍላጐት መወሰን እንዲቻል ከዋና ዋና መረጃ ተጠቃሚዎች አስተያየት የማሰባሰብ ሥራንና የሌሎች አገሮች ተሞክሮ በመፈተሽ የጥያቄዎች ዝርዝር ተዘጋጅቶ ለመ/ቤቱ የቆጠራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በማቅረብ እንዲጸድቅ ተደርጓል።

- የቆጠራው የእንግሊዝኛ፣ የአማርኛ፣ የገጠርና የከተማ አጭርና ረዥም መጠይቆች ዝግጅት ሥራ ተጠናቆ በሙከራ ቆጠራው ወቅት እንዲፈተሹ የተደረገ ሲሆን፣ በሥራው ላይ ለማሳተፉ ተቆጣጣሪዎች መመሪያዎች ተዘጋጅተዋል።

- የቆጠራውን መረጃ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለተጠቃሚዎች ለማሠራጨት የስካኒንግ ቴክኖሎጂ ጠቀሜታ ያለው መሆኑ ስለታመነበት ይህንን ቴክኖሎጂ ለ1999 የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ዝግጅት ለመጠቀም እንዲቻል ከወዲሁ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ስለ አጠቃቀሙ ልምድ ለመቅሰም የመ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ወደ ታንዛኒያና ጋና በመሄድ የልምድ ልውውጥ አድርገው ተመልሰዋል። በመስክ ጉብኝቱ ወቅት የተገኘውን ልምድ የመ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ለቀሪዎቹ የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የግማሽ ቀን ገለጻ በማድረግ ግንዛቤን ለማስጨበጥ ተሞክሯል።

- የስካኒንግ ቴክኖሎጂን በሙከራ ቆጠራ ለመፈተሽ የሚያስችል መጠይቆች ለስካኒንግ በሚያመች ሁኔታ የተቀረጸ ሲሆን የቆጠራና የተቆጣጣሪ መመሪያዎችን የማዘጋጀቱ ተግባር በመካሄድ ላይ ይገኛል።

- በ1999 ለሚካሄደው ቆጠራ የገንዘብና የሎጂስቲክ ድጋፍ ለማስገኘት ቀደም ሲል የተዘጋጀውን Strategy and Implementation Plan for Census 2007 የሚለውን ሰነድ በመከለስ ከተባበሩት መንግሥታት የስነ-ሕዝብ ጉዳይ ፈንድ ጋር በመተባበር ለጋሽ ድርጅቶችን በማነጋገር ለቆጠራው መሳካት ድጋፍ እንዲያደርጉ የመቀስቀስ ሥራ ከመሠራቱም ባሻገር የለጋሽ ድርጅቶች ስብሰባ እንዲደረግ የማስተባበር ሥራ ተካሄዷል።

### 3.2.2. የሕዝብና ቤት ቆጠራ የሙከራ ቆጠራን በሚመለከት

የሙከራ ቆጠራ ዓላማ በዋናው ቆጠራ ወቅት የሚከናወኑ ተግባራትን አነስ ባለ የቦታ ሽፋን በመሞከር ለዋናው ቆጠራ ልምድና ትምህርት ለማግኘት ነው። የሙከራ ቆጠራው ጠቀሜታ የተዘጋጀው የቆጠራ መጠይቅና መመሪያዎች ግልፅነት የተዘጋጁትን የቆጠራ ቦታ ካርታዎች ጥራት፣ በቆጠራው ወቅት የሚሠማራውን የሰው ሃይል ብቃት፣ በሙከራ ቆጠራው የሚሰበሰበውን የመረጃ ጥራት ለመገምገም ለቆጠራና ለሥልጠና የተመደበ ጊዜን ለማረጋገጥና ለመስክ ሥራው የታሰቡ የቅድመ ዝግጅት ስልቶችን ለመፈተሽ እንዲሁም ህብረተሰቡ ስለቆጠራው ያለውን ግንዛቤና የሚያደርገውን ትብብር አጥጋቢ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው። በዚሁ መሠረት፣

- ለሙከራ ቆጠራው የአሠልጣኞች ሥልጠና ከግንቦት 2-10/1998 የቆጣሪዎችና የተቆጣጣሪዎች ሥልጠና ከግንቦት 14-24/1998፣ በተመረጡ የቆጠራ ቦታዎች የቤተሰቦችና የቤቶች ምዝገባ ከግንቦት 27-30/1998 ድረስ ተካሄዶ የሙከራ ቆጠራው ከሰኔ 1-9/1998 ድረስ ሊጠናቀቅ ችሏል።

- ከላይ ለተዘረዘሩት ተግባራት የቆጠራ ዝርዝር መርሃ ግብር የሙከራ ቆጠራ መጠይቆችና መመሪያዎች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ ውለዋል።

### 3.2.3 ሁለተኛው ዙር የሥነ-ሕዝብና ጤና ጥናትን /DHS./ በተመለከተ

የዓለም አቀፍ የናሙና ጥናት ፕሮግራም አካል የሆነውን የሥነ-ሕዝብና ጤና ጥናት ባለፈው የበጀት ዓመት በአገሪቱ ለሁለተኛ ጊዜ ለማካሄድ በዕቅድ ተይዞ የመስክ ሥራው ከመጋቢት ወር 1997 አጋማሽ ጀምሮ እስከ ነሐሴ 30 ቀን 1997 ሲካሄድ ቆይቷል:: በዚሁ መሠረት በ1998 በጀት አመት የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት ተከናውነዋል::

- ከመስክ የተሞሉ ቅጾችንና መጠይቆችን ሁለት ዙር ኤዲትና ኮድ በማድረግ መረጃውን ወደ ኮምፒውተር ማስገባት፣ የመረጃ እርማት እና የመረጃ የማቀነባበር /Data Processing/ ሥራዎች በተያዘላቸው ጊዜ ተጠናቀው የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት በማዘጋጀት ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል::

- ከዓብይ ኮሚቴ (Steering Committee) ና የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ጋር በየጊዜው ግንኙነት በማድረግ በሥራ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን ለመፍታት ስብሰባዎችን ማዘጋጀት ተችሏል:: እንዲሁም ለጥናቱ ቴክኒካዊ እገዛ ከሚያደርገው (ORC – MACRO) በየወቅቱ /በስልክ፣ በኢሜል፣ በአካል... ወዘተ/ በመገኘት የጥናቱ ቀሪ ሥራዎች በተያዘላቸው ፕሮግራም መሠረት ስለሚጠናቀቁበት መንገድ አስፈላጊውን መረጃ ለማቅረብ ተሞክሯል::

- በጥናቱ የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት ላይ የተሰጡ አስተያየቶችን በማካተት የዋናው ሪፖርት ሥራ የተጀመረ ሲሆን፤ ለሪፖርቱ የተዘጋጁት ሠንጠረዦች ተገምግመው በአሁኑ ወቅት ከአቢይ ኮሚቴው የተሰጡት አስተያየቶች ተካተው ዋናው ሪፖርት ለሕትመት ዝግጁ ሆኗል::

- በጥናቱ ከተሰበሰቡት መረጃዎች መካከል አንዱ የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መረጃ በመሆኑ ከዋና መረጃ ተጠቃሚዎች ጋር በተያዘው ፕሮግራም መሠረት ከMACRO ጋር በመሆን የ2 ቀን ስብሰባ ተካሄዷል:: በስብሰባው ወቅት በተነሱ ቴክኒካዊ ጥያቄዎች መሠረት በተከታታይ ለ3 ሳምንታት በተለያየ ደረጃ ስብሰባዎችና ውይይቶች ተካሄደዋል::

- የሥነ ሕዝብና ጤና ጥናትን አስመልክቶ የተባበሩት መንግሥታት የሕዝብ ጉዳይ ፈንድ (UNFPA) ለለጋሽ አገሮችና ድርጅቶች በየጊዜው የሚቀርበው የሥራ ሂደት ሪፖርት ማዘጋጀት እና ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ተከናውኗል::

### 3.2.4 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስን በተመለከተ

- ወደፊት በአገር አቀፍ ደረጃ የሚቋቋሙት የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓቶች በሕግ፣ በቴክኒክ፣ በአስተዳደር፣ በበጀትና በሰው ኃይል ድልድል በኩል ሊያጋጥሙአቸው የሚችሉ ችግሮችን ለማጥናት የሚያስችል በተባበሩት መንግሥታት የሕጻናት መረጃ ድርጅት (UNICEF) የገንዘብና በጽ/ቤቱ የቴክኒክ ድጋፍ በደቡብ ኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በአማራና በትግራይ ክልሎች ሞዴል የምዝገባና ስታቲስቲክስ ፕሮግራሞች የሥራ ሂደት ላይ በመስክ በመገኘት ግምገማ ተካሂዷል::

- የዚህን ፕሮግራም አጠቃላይ ሂደት መከታተልና መገምገም እንዲቻል የመ/ቤቱ ባለሙያዎች በተለያዩ ቡድኖች በመከፋፈል ከሰኔ 25/1997 እስከ ሐምሌ 1/1997 በደቡብ ኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በ14 የገጠርና የከተማ ቀበሌዎች ፣ በአማራ ክልል ከሐምሌ 20 ቀን 1997 – ሐምሌ 29 ቀን 1997 በክልሉ ለሞዴል የምዝገባ ፕሮግራሙ ከተመረጡት 32 የገጠርና የከተማ ቀበሌዎች ውስጥ በ27ቱ የመስክ ጉብኝት ተደርጓል::

- ከዚህም ሌላ ሁለት አባላት ያሉት ቡድን በትግራይ ክልል በተለያዩ ወረዳዎች በመካሄድ ላይ ያለውን ሞዴል የምዝገባና ስታቲስቲክስ ፕሮግራም በቴክኒክ፣ በአስተዳደርና በአፈጻጸም ረገድ ባጋጠሙት ችግሮችና የተገኙ ልምዶችን በመገምገም መስከረም 7 ቀን 1998 በመቀሌ ከተማ በተካሄደ ስብሰባ ላይ ተሳትፏል:: በዚህም ወቅት በስብሰባው ላይ ቡድኑ በምዝገባ ቅጾቹ ላይ ስለተደረጉ ለውጦችና በሞዴል ፕሮግራሙ ላይ ስለተሰራው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ኮምፒውተር ፕሮግራም ማብራሪያ ሰጥቷል::

- በሦስቱም ክልሎች በተካሄዱ ጉብኝቶች ቡድኖች በመስክ በመገኘት ሥራውን ከሚያከናውኑ መዝጋቢዎች፣ ከአስተባባሪዎችና ከየወረዳው ሥራ አስፈጻሚዎችና ከክልል የሥራ ኃላፊዎች ጋር በቴክኒካዊ፣ በአስተዳደራዊና የበጀት ጉዳዮች ላይ በመወያየት የክልሉን ሞዴል የምዝገባና ስታቲስቲክስ ፕሮግራም በመገምገምና የፕሮግራሙን ደካማና ጠንካራ ጐኖች የመለየት ተግባራትን የሚዳስስ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው አካላት አቅርቧል::

- ለሞዴል የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ፕሮግራሙና ወደፊት በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚቋቋሙት የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓቶች የሚያገለግሉ የምዝገባ አፈጻጸም /መዝጋቢዎች መመሪያ/ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻ ፍቺ የክብር መዝገቦችና የምስክር ወረቀቶችን የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓቶች ሞዴል ፕሮግራም የአስተዳደርና የአደረጃጀት አፈጻጸም መመሪያ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ሥርዓቶችን በመቋቋም የምዝገባ ተቋማትና ዋንኛ ተባባሪ ድርጅቶች ዋና ዋና የተግባር ዘርፎች መመሪያ፣ አገር አቀፍ የድርጊት መርሃ ግብርን የማረምና የማሻሻል ተግባራት ተከናውነዋል::

- ከተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መረጃ ድርጅት ጋር ተከታታይ ግንኙነት በማድረግ እ.ኤ.አ በ2005 በሦስት ክልሎች የተጀመረው ሞዴል ፕሮግራም በ2006 ለመቀጠል እንዲቻል ከክልሎቹ ጋር በመተባበር የፕሮጀክት ዶክመንት ተዘጋጅቶ ለድርጅቱ ቀርቧል:: እንደዚሁም ሞዴል ፕሮግራሙን በሌሎች አዳዲስ ክልሎች ስለሚጀመርበት ሁኔታ ከድርጅቱ ጋር ምክክር ተደርጓል:: በዚሁ መሠረት የኦሮሚያ ክልል በሞዴል ፕሮግራሙ እንዲታቀፍ ከክልሉ ፋይናንስ ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ለድርጅቱ የሚቀርብ የፕሮጀክት ዶክመንት ለማዘጋጀት ለቢሮው የቴክኒክ እገዛ ተደርጓል::

- ከሞዴል ክልል መስተዳድሮች የተሰበሰበውን መረጃ በኮምፒውተር ለማስገባትና በቫይታል ስታቲስቲክስ መረጃዎችን ለማጠናቀር ቅድመ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ሥራ በመካሄድ ላይ ይገኛል:: እንዲሁም

ለወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርአቶችን በሚመለከት በአገር አቀፍ ደረጃ የሁለት ቀን የግንዛቤ ማስጨበጫ አውደ ጥናት ተካሄዷል፡፡

## 4. የ1998 በጀት ዓመት የፊዚካል ሥራ አፈጻጸም

በ1998 በጀት ዓመት መ/ቤቱ ለሚያካሂዳቸው አዳዲስ ጥናቶችንና ከ1997 የተሸጋገሩ ቀሪ ሥራዎችን ለማከናወን በዕቅድ መያዙንና በበጀት ዓመቱ ያከናወናቸውን ሥራዎች በዝርዝር ቀርበዋል፡፡ የእነዚህን ጥናቶች የፊዚካል አፈፃፀም በተመለከተ ደግሞ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 1 የ1998 በጀት ዓመት የፊዚካል ሥራ አፈጻጸም

| ተራ ቁ.. | የጥናቱ ዓይነት | ጥናቱ የሚገኝበት ደረጃ | እስከ 1998 በጀት ዓመት መጨረሻ የተከናወነ | የ1998 በጀት ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም |
| 1 | የ1998 የግብርና ናሙና ጥናት | | | | | |
| 1.1 | የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት | አዲስ | 6.49 | 93.51 | 93.51 | 100 |
| 1.2 | የግብርና ምርት ናሙና ጥናት የመኸር ወቅት | | | | | |
| | • የታረሰ መሬት ናሙና ጥናት | አዲስ | 6.49 | 93.51 | 85.50 | 91 |
| | • የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ | አዲስ | 6.49 | 93.51 | 85.50 | 91 |
| | • የመሬት አጠቃቀም | አዲስ | 6.49 | 93.51 | 85.50 | 91 |
| 1.3 | የቤት እንስሳት ዶሮና የንብ ቀፎዎች ጥናት | አዲስ | 6.43 | 93.57 | 93.57 | 100 |
| 1.4 | የግብርና ምርት ናሙና ጥናት የበልግ ወቅት | አዲስ | 6.43 | 83.50 | 57.50 | 69 |
| 1.5 | የሰፋፊና መካከለኛ የድርጅት እርሻዎች ጥናት | አዲስ | 6.43 | 93.51 | 66.00 | 70 |
| 1.6 | የ1997 የግብርና ምርት ናሙና ጥናት በበልግ ወቅት | ነባር | 65.00 | 35.00 | 35.00 | 100 |
| 1.7 | የ1997 የሰፋፊና መካከለኛ የድርጅት እርሻዎች ጥናት | ነባር | 65.00 | 35.00 | 25.00 | 71 |
| 2 | የግብርና ውጤቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት | አዲስ | 3.00 | 97.00 | 93.82 | 96 |
| 3 | የችርቻሮ ዋጋ ጥናት | አዲስ | 3.00 | 97.00 | 95.00 | 98 |
| 4 | የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት | ነባር | 90.00 | 10.00 | 10.00 | 100 |
| 5 | የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት | ነባር | 65.00 | 35.00 | 25.00 | 71 |
| 6 | ዓለም አቀፍ የንጽጽር ፕሮግራም በአፍሪካ | ነባር | 6.36 | 92.27 | 82.27 | 89 |
| 7 | ወቅታዊ የማምረቻ፣ የንግድና የአገ.ሰጪ. ድርጅት | አዲስ | - | 100.00 | 100.00 | 100 |
| 8 | የማምረቻ ኢንዱስትሪ የምርት ዋጋ ኢንዴክስ | አዲስ | 15.00 | 85.00 | 85.00 | 100 |
| 9 | የአነስተኛ ማምረቻ አንዱስትሪ ጥናት | አዲስ | - | 100.00 | 75.00 | 75 |
| 10 | የ1997 የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱ ጥናት | አዲስ | - | 60.00 | 60.00 | 100 |
| 11 | የማዕድንና ቁፋሮ ጥናት | አዲስ | - | 14.52 | 14.52 | 100 |
| 12 | የኮንስትራክሽን ጥናት | አዲስ | - | 86.00 | 86.00 | 100 |
| 13 | የ1996 የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱ. ጥናት | ነባር | 65.00 | 35.00 | 35.00 | 100 |
| 14 | የ1997 የሰው ኃይል ጥናት | ነባር | 65.00 | 35.00 | 35.00 | 100 |
| 15 | ለኤች.አይ.ቪ. በምክንያት የሚጠቀሱ ባህርያት ጥናት | ነባር | 65.00 | 35.00 | 25.00 | 71 |
| 16 | ተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናት | አዲስ | - | 100.00 | 80.00 | 80 |

## 5. ሜቶዶሎጂ አገልግሎት

በዚህ የሥራ ክፍል መ/ቤቱ በየዓመቱ ለሚያካሂዳቸው የተለያዩ የስታቲስቲክስ ጥናቶች የሚያገለግሉ የአሠራር ዘዴዎችና የአፈጻጸም መመሪያዎች እንዲሁም ለጥናቶች የሚያገለግሉ መጠይቆችና ቅጾች ጥራት፣ ብቃትና ወካይነታቸውን የማረጋገጥ ሥራ ይከናወናል:: በዚሁ መሠረት በበጀት ዓመቱ የሚከተሉት ተግባራት ተከናውነዋል::

### 5.1 የሳምፕሊንግ ሜቶዶሎጂን በተመለከተ

- የ1997 የሰው ኃይል ጥናትን በሚመለከት ለማባዣ የሚያገለግሉ በየቆጠራው ቦታ የተመዘገቡ ቤተሰቦች ብዛት ከየቆጠራ ቦታው የመልቀም ሥራ ተካሂዶ የ Weight እና Rate ፎርማት ተዘጋጅቶ የተጠናቀቀ ሲሆን የሜቶዶሎጂ ሪፖርት ተከናውኖ ለሚመለከተው ክፍል ተላልፏል::

- የ1996/97 የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት Weight እና Rate ተዘጋጅቷል::

- የ1997 ዓ.ም የበልግ ወቅት ግብርና ናሙና ጥናት፣ ለመሬት ስፋትና ምርት መጠን ጥናት፣ ለእርሻ ሥራ ሁኔታ ጥናት Weight እና Rate ዝግጅት እንዲሁም የናሙና ጥናቱ አስተማማኝነት ግምገማና የሜቶዶሎጂ ሪፖርት ዝግጅት ሥራ ተጠናቋል::

- የ1998 ዓ.ም የግብርና ናሙና ጥናት ቆጠራ ቦታዎችንና የሠፈራ መንደሮችን ዝርዝር የያዘ ኮድ ቡክ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው ተሠራጭቷል:: ለዚሁ የናሙና ጥናት የታቀደው የተሻሻለ የአሠራር ዘዴ መሠረት አዲስ የናሙና ቦታዎች ብዛት ድልድል በዞን ደረጃ ተከናውኗል:: በአዲስ መልክ ሥራውን ለማካሄድ በታቀደው መሠረት ስለቤተሰብ አመዘጋገብና ናሙና አመራረጥ ለመረጃ ሰብሳቢዎች ተቆጣጣሪዎች መመሪያ ተዘጋጅቷል::

- በኢኮኖሚያዊ ድርጅቶች ቆጠራ ወቅት ከመረጃ ማቀነባበሪያ የተገኙ የቆጠራ ቦታዎችን ዝርዝር ከካርቶግራፊ ክፍል ካለው ካርታና መግለጫ ካላቸው የቆጠራ ቦታዎች ዝርዝር ጋር እንዲገናዘብና ልዩነቶች እንዲለቀሙ የማድረግ ሥራ ተካሄዷል::

- ለ1998 ዓ.ም ተከታታይ ሥራ ስምሪት ጥናት የአመዘጋገብና የአመራረጥ መመሪያ ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው የተላለፈ ሲሆን፣ የናሙና ምርጫና የቆጠራ ቦታ ካርታ ዝግጅት ተደርጓል::

- የ1998 ዓ.ም የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎችና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ጥናት የሳምፕሊንግ ዲዛይንና የድርጅቶች አመዘጋገብና አመራረጥ መመሪያ ዝግጅት ሥራ ተጠናቋል:: በከተሞች የሚጠኑ ድርጅቶችን የመምረጥ ሥራ የተከናወነ ሲሆን፣ ስለድርጅቶቹ አመዘጋገብ መምሪያ ተዘጋጅቶ ሥልጠና ተሰጥቷል:: እንዲሁም ለመስክ ሥራ፣ ለኤዲቲንግና ኮዲንግ የሚያስፈልገውን ኮድ ቡክ የማዘጋጀቱ ሥራ ተጠናቋል::

- የ1997 ዓ.ም ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ባህሪ ቅኝት ጥናትን በሚመለከት የተማሪዎችን Weight እና Rate ለማዘጋጀት የሚያስፈልግ የፎርማት ዝግጅት ሥራና የ Weight እና Rate ዝግጅት ሥራም ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል::

- የ1998 የሰብል ትንበያ ጥናት Weight እና Rate የተዘጋጀ ሲሆን የሜቶዶሎጂ ሪፖርት ዝግጅትም ተጠናቋል::

- የ1998 ዓ.ም የቤት እንስሳት ናሙና ጥናት Weight እና Rate ዝግጅት ሥራን በማጠናቀቅ በኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ ወቅትም የአካባቢ መለያን በሚመለከት ክትትል በማድረግ የእርምት ሥራ ተካሄዷል:: እንዲሁም የውጤት አስተማማኝነት ግምገማ ተከናውኖና ሪፖርቱ ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ተላልፏል::

- የ1998 ተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናትን በሚመለከት ቀደም ሲል የተመረጡ ናሙናዎችን በአዲሱ የቀበሌ አደረጃጀት መሠረት የማስተካከልና የ527 የቆጠራ ቦታ ካርታዎች ዝግጅት ተጠናቆ ለየቅ/ጽ/ቤቶች

ተሠራጭተዋል፡፡ በተጨማሪም የቤተሰቦች አመዘጋገብና አመራረጥ መመሪያ ተዘጋጅቶ ሥልጠናው ተሰጥቷል፡፡

- የ1998 የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት የዲዛይንና በየከተሞች የሚጠኑ ድርጅቶችን የመምረጥ ሥራ ተካሄዶ ለሚመለከተው የተላለፈ ሲሆን፣ የኮድ ቡክ፣ Weight እና Rate ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ እንዲሁም የ1998 ዓ.ም ለተካሄደው የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት Weight እና Rate ዝግጅት የሚያስፈልጉ ዝግጅቶችን በማጠናቀቅ የኮድ ቡክ ዝግጅት በኤዲቲንግ ወቅት ክትትልና ዕርማት የማከናወን ሥራም ተከናውኗል፡፡

- ለ1999 ዓ.ም ህዝብና ቤቶች ቆጠራ የሙከራ ጥናት የሚያስፈልጉ የናሙናዎችን ብዛት በየከተማውና ወረዳው የመምረጥ ሥራ ተጠናቋል፡፡ እንዲሁም የቤተሰቦች መመዝገቢያ በቆጠራ ቦታ ደረጃ የሚጠየቁ ጥያቄዎችንና በዋናው መጠይቅ የሚካተቱ ሁለት ምዕራፎችን አጠቃላይ ይዘት ቅጾችን፣ በማዘጋጀትና የመጠይቆች የአሞላል መመሪያ ዝግጅት በአብዛኛው ተከናውኗል፡፡

- ለ1999 ዓ.ም የግብርና ናሙና ጥናት እና የገጠር ኢንቨስትመንት ሁኔታ ጥናት የሚያስፈልጉ የዲዛይንና የአመዘጋገብ/ አመራረጥ መመሪያ ዝግጅት ሥራ ተከናውኗል፡፡

## 5.2 ስታንዳርድና መዛግብት አያያዝን በተመለከተ

- ለወረዳ ኔት ፕሮግራም የተሰበሰቡ ፎርማቶች ጽንሰ ሃሳቦችና ፍችዎቻቸውን በየዘርፉ በመተንተን ትርጉማቸው በግልጽ የተቀመጡትንና ያልተቀመጡትን የመለየት ሥራ ተከናውኗል፡፡

- የሥራና የኢንዱስትሪ ምደባዎችን በየመምሪያዎቹ ለሚያከናውኑት አይዚክ /ISIC/ እና አይስኮ (ISCO) ጋር ለማነጻጸር የሚያገለግል ዶኩመንት ተዘጋጅቷል፡፡

- ለአርብቶ አደር አካባቢ የቅድመ ቆጠራ ጥናት ለማካሄድ የሚያስፈልግ ዶኩመንት ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል::

- አጠቃላይ በስታንዳርድ ደረጃ ሊያገለግሉ የሚችሉ ጽንሰ ሃሳብና ፍችዎቻቸው የማዘጋጀቱ ሥራ ተከናውኖ በአሁኑ ወቅት ወደ አማርኛ የመተርጐም ሥራ በመካሄድ ላይ ይገኛል::

## 5.3 ካርቶግራፊን በተመለከተ

- ከተለያዩ መ/ቤቶች የከተሞችን ማስተር ፕላን በትውስት በማምጣት የ42 ከተሞች ማስተር ፕላን አራት አራት ኮፒ ተዘጋጅተው ወደ መስክ ለሥራ ተልከዋል::

- የቆጠራ ካርታ የሚያስፈልጋቸውን ቀሪ ወረዳዎች በመለየትና የሚሸፍናቸው የቶፖግራፊ ካርታ በማዘጋጀት የ47 ወረዳ ካርታዎች ለሚመለከታቸው ጽ/ቤቶች ተልከዋል:: እንዲሁም የ311 ወረዳ የቆጠራ ካርታዎችና ተዛማጅ ዶክመንቶች ርክክብ ተፈጽሟል::

- ለተለያዩ ጥናቶች የ830 ቆጠራ ቦታዎች ካርታ ኮፒ ተደርጐ ለሚመለከተው ክፍል ተሰጥቷል::

- በስምንት ዞኖች ለሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ የሚያገለግሉ ባለ 1:50,000 መስፈርት የቶፖግራፊ ካርታዎችን በመለየት ተገዝተው ለሚመለከታቸው ቅ/ጽ/ቤቶች ተሠራጭተዋል:: የ282 የወረዳ ካርታዎች ለውጭ ተገልጋዮች ተሸጠዋል::

# 6. መረጃ ማቀነባበርን በተመለከተ

መ/ቤቱ በየዘመኑ የሚያካሂዳቸውን ጥናቶች መረጃ በዚህ የሥራ ክፍል ውስጥ የማቀነባበር ተግባር ይካሄዳል የሥራ ክፍሉ በዋነኛነት የሚያካሂዳቸው ሥራዎች ከመስክ የተመለሱ የጥናት ዶክመንቶችን በስርዓት በመደርደር ኤዲትና ኮድ መስጠት፣ መረጃዎቹን ወደ ኮምፒውተር ማስገባት፣ በተለያዩ የኮምፒውተር ፕሮግራሞች በመጠቀም የመስመራዊ መምሪያዎች በሚጠይቁት ሁኔታ

ለሪፖርት በሚያመች ሁኔታ በሠንጠረዥ ማቅረብ ሲሆኑ፤ በበጀት ዓመቱና ባለፉት ዓመታት በመስክ መረጃ የተሰበሰበላቸውን ጥናቶች አጠቃላይ የመረጃ ማቀነባበር አገልግሎት ሰጥቷል፡፡ በመሆኑም በበጀት ዓመቱ የሚከተሉትን ሥራዎች አከናውኗል፡፡

## 6.1 የኤዲቲንግና ኮደንግና ዳታ ኢንትሪ

በ1997 ዓ.ም የመረጃ መሰብሰብ ተግባር የተከናወነላቸው አምስት የተለያዩ ጥናቶችን ማለትም ወርሃዊ የዋጋ ጥናቶች፣ የቤተሰብ ገቢ፣ፍጆታና ወጪ ጥናት፣ የሰው ኃይል ጥናት፣ የበልግ ጥናት፣ የሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች ጥናት እንዲሁም የኤች.አይ.ቪ /ኤድስ የባህሪ ቅኝት ጥናት መረጃ የኤዲቲንግ፣ኮዲንግና የዳታ ኢንትሪ ሥራ ተከናውኗል፡፡

እንዲሁም በ1998 ዓ.ም የተከናወኑ የሰብል ትንበያ ጥናት፣ የቤት እንስሳት ጥናት፣ የሠፈራ ጣቢያዎች የግብርና ናሙና ጥናት፣ የወቅታዊ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣ የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት የበልግ ናሙና ጥናት፣ የተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናትና ሌሎችም ጥናቶች የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግና የዳታ ኢንትሪ ሥራ ተከናውኗል፡፡

## 6.2 የሠንጠረዥ ዝግጅት

- በበጀት ዓመቱ የጥናቶችን ሪፖርት ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ የኮምፒውተር ፕሮግራሞች ተዘጋጅተው የጥናቶችን ውጤት የሚያሳዩ ሠንጠረዦችና የውጤት አስተማማኝነት መለኪያ /CV/ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ተሰጥቷል፡፡ እነዚህም በ1997 ዓ.ም የመረጃ መሰብሰብ ተግባር ለተካሄደላቸው ለሰባት ጥናቶችና በ1998 ዓ.ም ለተከናወኑ ስድስት ጥናቶች አገልግሎቱ ተሰጥቷል፡፡

- በሌላ በኩል መረጃዎችን ወደ SPSS Format በመለወጥ ለተጠቃሚዎች በሚያመች መንገድ ለማዘጋጀት በታቀደው መሠረት የ1996 የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት፣ የ1997 አጠቃላይ የእርሻ ሥራ ሁኔታ ጥናት፣ የ1997 የታረሰ መሬትና የምርት መጠን ጥናት፣ የ1997 የመሬት አጠቃቀም ጥናት፣ የበልግ ወቅት ጥናት፣ የ1997 የአምራቾች ዋጋ ጥናት፣ የ1996

የትላልቅና መካከለኛ ኢንዱስትሪ ጥናት፣የ1997 የአምራቶች ዋጋ ጥናት፣ የ1997 የሆቴሎች ዋጋ ጥናት፣ የ1997 እና 1998 የቤት እንስሳት ጥናት፣ ከ1988-1993 ያለው የቤት እንስሳት ጥናት መረጃዎችን ወደ SPSS Format የመለወጥ ሥራ ተጠናቋል::

## 6.3 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት

- በመ/ቤቶች፣ በድርጅትና በግለሰብ ደረጃ ለቀረቡ የመረጃ ጥያቄዎች ምላሽ ተሰጥቷል::

- እ.ኤ.አ የ2005 የሩብ ዓመት የትላልቅና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ጥናት Indicators በEthioInfo Data Base ሥራ ተጠናቋል::

- እ.ኤ.አ የ2000 Demography and Health Survey (DHS) መረጃ Indicators በEthio Info Data Base የማዘጋጀቱ ሥራ ተጠናቋል:: እ.ኤ.አ የ2004 እና የ2005 የታረሰ መሬት ስፋትና የምርት መጠን ጥናት መረጃ አመልካች፣ እንዲሁም 2004 እና የ2005 የቤት እንስሳት ጥናት Indicators EthioInfo database የማዘጋጀቱ ሥራ ተጠናቋል፣

# 7. ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂን በተመለከተ

- በዕቅድ ዘመኑ ለICT አቅም ግንባታ ከUNDP ተገዝተው የመጡ ዕቃዎች አስፈላጊውን የኮንፊገሬሽን ሥራ በመሥራት ዕቃዎችን በመረከብ ሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርገዋል::

- የመ/ቤቱ ድረ-ገጽ ተጠናቆና ተመርቆ ሥራ ላይ የዋለ ሲሆን በዚሁ ድረ-ገጽ መ/ቤቱ ውስጥ ባለው Server Host በማድረግ በየትኛውም ዓለም ያለ ተጠቃሚ እንዲያገኘው የሚያስችለውን የDomain Registration እና Public IP ከኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን በመግዛት ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል::

- በማዕከላዊ የመረጃ ማዕከል ተከማችተው ከነበሩ ጥናቶች ውስጥ የ1996፣ 1998፣ 2002፣ 2004፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ደህንነት ጥናቶች፣ የ2003 እና

2004 የእንስሳት ጥናት፣ የ1995 -2000 እና 2003-2004 የግብርና ናሙና ጥናትና የ2003 Internal Sector የ1996 - 2004 የትላልቅና የመካከለኛ ኢንዱስትሪ ጥናቶች፣ የ2002 አነስተኛና ጥቃቅን ኢንዱስትሪ የ2001 የህጻናት የሥራ ሥምሪት ጥናት፣ የ1995-2000 የቤተሰብ ገቢ ፍጆታ ወጪ ጥናት፣ የ1999 የሰው ሃይል ጥናት፣ የ2003-2004 ተከታታይ የሰው ኃይል ጥናት በData Management Toolkit በመጠቀም CD እና በድረ ገጽ መሠራጨት በሚችሉበት መንገድ ተደራጅተው እንዲቀመጡ ተደርጓል::

- የመ/ቤቱን የሰው ኃይል የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ዘመናዊ አሠራርን የተከተለ እንዲሆን ወደ ኮምፒውተር የማስገባት ሥራ የተከናወነ ሲሆን ለሚመለከታቸው ክፍሎችም ሥልጠና ተሰጥቷል::

- ብዛት ያላቸውን ኮምፒውተሮች መለዋወጫን የመቀየር ሥራ፣ የኮንፊገሬሽን ሥራ እንዲሁም ለ58 ኮምፒውተሮች እና ለ 3 ፕሪንተሮች ጥገና ተደርጐላቸው ሥራ ላይ የዋሉ ሲሆን የ8 ኮምፒውተሮች ሜሞሪ እንዲያድግ ተደርጓል::

- የመ/ቤቱን የመረጃ ክምችትና ስርጭት እንዲሁም የኔት ዎርክ አስተዳደር በተቀላጠፈ መንገድ ለማካሄድ እገዛ የሚያደርግ የአንድ ሳምንት ሥልጠና ከውጭ በመጡ ባለሙያዎች የተሰጠ ሲሆን 76 ተጨማሪ ኔትወርትክ በመ/ቤቱ በተለያዩ ቢሮዎች ተዘርግተዋል::

- የጂኦግራፊ ኢንፎርሜሽን ሲስተም የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን በማካሄድ በቆጠራ ካርታ ሥራ በGPS አማካይነት ተጠናቅረው የመጡ መረጃዎች የዳታ ቤዝ (Data Base) ምሥረታ በመከናወን ላይ ይገኛል:: እንደዚሁም የ2004 የማህበራዊ ደህንነት ጥናቶችን በክልልና አገር አቀፍ የተወሰኑ አመልካቾች (Indicators) በመውሰድ በአትላስ ለማሳየት ተሞክሯል:: በተጨማሪም የ170 ወረዳዎች Coordinate የማስገባት ሥራ ተጠናቋል::

- መ/ቤቱ የተቀላጠፈ አስተማማኝና ትክክለኛ መረጃ ለተጠቃሚዎች በሚፈልጉት ፎርማት ለማድረስ ካለው ራዕይ በመነሳት የትላልቅና መለስተኛ ኢንዱስትሪ ጥናትን መሠረት በማድረግ Data base requiremente gathering

አልቆ Data base Structure ተጀምሮ አብዛኞቹ የTables and columns ሥራ የተለየ ሲሆን አዲስ በሚወጣው መጠይቅ ላይ የሚካተቱ ጉዳዮችንና አዳዲስ ጥያቄዎችንም ለማካተት ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

- በመ/ቤቱ ድረ-ገጽ ላይ ወቅታዊ የሆኑ መረጃዎች እንዲካተት የተደረገ ሲሆን የመ/ቤቱን አቅም ለመገምባት ከዓለም ባንክ በኩል ለሚከናወኑት ከ Trust Fund እና STATCAP ድጋፍ ለማስገኘት የሚረዳ ዶኩመንት በማዘጋጀት ለሚመለከተው ቀርቧል፡፡

- በርካታ ጥሬ መረጃዎችና ሪፖርቶች ጥያቄ ላቀረቡ መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ደርጅቶች ለተመራማሪዎችና ለተማሪዎች ተገቢው አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡

## 8 <u>ሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ጽ/ቤት</u>

### ሀ. <u>በኤጀንሲው የተከናወኑ ልዩ ልዩ የማሻሻያና የአቅም ግንባታ ሥራዎች</u>

- በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር ለሚገኙ የስታቲስቲክስ መረጃ ተጠቃሚዎች በያሉበት የጥናት ውጤቶችን በዌብ ሣይት (www.csa@ gov.et) ማሰራጨት ተጀምሯል፡፡ በተጨማሪም በUNICEF እርዳታ EthioInfo የተባለውን ሶፍት ዌር ከመረጃ መረብ ጋር በማገናኘት መረጃዎችን ለተጠቃሚዎች በቀላሉ ማሰራጨት ተችሏል፡፡

- የመረጃ ዴስክ የሥራ ክፍል 658 የውጭ ተገልጋዮችን በመቀበልና 6,703 ኢትዮጵያውያንን በማስተናገድ ከቤተ መጻሕፍቱ፣ ከሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎችና ባለሙያዎች ጋር በማገናኘት አገልግሎቱን በቀላሉ እንዲያገኙ አስችሏል፡፡

- በቤተ መጻሕፍቱ ውስጥ የፎቶ ኮፒ አገልግሎት በመጀመሩ ተገልጋዮች የሚፈልጓቸውን መረጃዎች ብቻ ኮፒ በማድረግ እንዲወስዱ በማስቻሉ ቀልጣፋ አገልግሎት ከማግኘታቸውም ባሻገር ሙሉ ሪፖርቱን ለመግዛት ከሚያወጡት ወጪ ነፃ ሆነዋል፡፡

- የሠራተኛውን የመፈጸም አቅም ለማጐልበት ሁለት የኦዲት አገልግሎት ሠራተኞች በውስጥ ኦዲት አሠራር ላይ በኢትዮጵያ ሥራ አመራር አንስቲትዩት፣ ሦስት ሠራተኞች ደግሞ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እንዲሰለጥኑ ተደርጓል፣ 11 ከልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች የተውጣጡ ሠራተኞች በኮምፒውተር መሠረታዊ አጠቃቀም ማለትም በWord, Excel እና Access በግል ተቋም የሰለጠኑ ሲሆን፣ አምስት ባለሙያዎች በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 9 ባለሙያዎች ደግሞ በውጭ ሀገር ለማስተርስ ዲግሪ እየሰለጠኑ ይገኛሉ:: በተጨማሪ በመ/ቤቱ ባለሙያዎች ለ100 የኦዲት፣ የሂሣብ ሠራተኞች፣ የገንዘብ ያዥና የንብረት አስተዳደር ሠራተኞች የሙያ የማሻሻያ ሥልጠና ተሰጥቷል::

- መ/ቤቱ ለሥራ አመች የሆነ አደረጃጀት እንዲኖረው ለማድረግ በአዲሱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል ፍላጐት መሠረት የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ የመስመራዊ መምሪያዎች፣ አገልግሎቶች፣ የሰው ሃብትና ሥራ አመራር መምሪያንና የፋይናንስ መምሪያን የሥራ መደቦች በተፈለገው ደረጃ አጽድቆ የመለሰ ሲሆን፣ የቴክኒክና ንብረት አስተዳደር አገልግሎትን በሚመለከት ደረጃው ዝቅ ብሎ በመመደቡ እንደገና እንዲታይ ጥያቄ ለኤጀንሲው ቀርቧል:: በሌላ በኩል በተፈቀዱት የሥራ መደቦች የሰው ኃይል ለመመደብ ዝግጅት እየተደረገ ነው::

- በመኪና አጠቃቀምና ጥገና በፋይናንስ አጠቃቀምና ወጪ ማስረጃ አቀራረብ፣ ንብረት አስተዳደር፣ ስለ ፐርሶኔል ሥራዎች አፈጻጸም፣ ስለመረጃ ጥራትና ቁጥጥር በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ ማኔጅመንቱ ከ25 ቅ/ጽ/ቤቶች ኃላፊዎች ጋር ተወያይቶ አስተዳደራዊ ውሳኔ ሰጥቷል::

- በመ/ቤቱ ተደጋጋሚ የስርቆት ተግባር የተፈፀመ በመሆኑ ድርጊቱን አስቀድሞ ለመከላከል እንዲቻል የዳሰሳ ጥናት ተከናውኖ የመፍትሄ አቅጣጫ ለማስቀመጥ ምክክር እየተካሄደ ነው::

ለ. <u>መሠረታዊ የአሠራር ማሻሻያ ሥርዓት /BPR/ ጥናትን በተመለከተ</u>

- የአሠራር ማሻሻያ በማድረግ በአጭር ጊዜ ውስጥ የተገልጋዩን ፍላጐት ማርካት ይችላል ተብሎ በታመነበት በግብርናና በመረጃ ክምችትና ስርጭት የሥራ ክፍሎች ላይ የተጀመረው BPR በአሁኑ ጊዜ ለመረጃ ክምችትና ስርጭት የተቀየሰው ማሻሻያ በመተግበር ላይ ሲሆን፤ የግብርናው ዘርፍ የነበሩበትን ችግሮች የመለየትና መፍትሄዎች የመቀየስ እንደዚሁም ለማሻሻያው ትግበራ መርሃ-ግብር የማዘጋጀት ሥራዎች ተከናውነዋል::

- በእነዚህ የሥራ ክፍሎች በተሠሩት ሥራዎች ላይ የበላይ ኃላፊዎች ከመምሪያና ከአገልግሎት ኃላፊዎች ጋር ተወያይተዋል:: ቀሪው የግብርናውን ለበላይ አስተባባሪና ገምጋሚ ኮሚቴ አቅርቦ አስተያየት መቀበል ይሆናል::

- በሌሎች የሥራ ክፍሎች ከላይ በተጠቀሱት የሥራ ክፍሎች የተዘጋጁትን ማሻሻያዎች በሞዴልነት በመጠቀም ሠራተኞችን ባሣተፈ ሁኔታ የየራሣቸውን BPR እየሠሩ ይገኛሉ:: አጠቃላይ ያሉበት ደረጃ በሠንጠረዥ 2 ላይ ቀርቧል::

- ኤጀንሲው ውጤት ተኮር ዕቅድን ከሐምሌ 1 ቀን 1998 ዓ.ም ለመጀመር አስቦ የተንቀሳቀሰ ቢሆንም ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ከ1999 ዓ.ም ከሚካሄደው የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ሥራን ከማጠናቀቅ አኳያ በተሰጠ ገንቢ አስተያየት ከ1999 ሐምሌ 1 ቀን ጀምሮ ለመጀመር ተወስኗል:: ሆኖም የተጠናቀቁትን የ BPR ሥራዎች ሥራዎች ከሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ለተመደቡ ባለሙያዎች በማቅረብ ለማስገምገም ዝግጅት እየተደረገ ነው::

# የሥራ ክፍሎች በBPR ሥራ የሚገኙበት ደረጃ

| ተራ ቁ | የሥራ ዘርፎች | መረጃ በማሰባሰብ ደረጃ | ችግሮችን በመለየት ደረጃ | ማሻሻያዎችን በመቀየስ ደረጃ | ማሻሻያዎችን በመተግበር ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የተፈጥሮ ሀብትና ግብርና ስታቲስቲክስ መምሪያ | ✔ | ✔ | ✔ | ✕ |
| 2 | የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማት ማስተባበሪያ መምሪያ | ✔ | ✔ | ✔ | ✔ |
| 3 | የአካባቢ ጽ/ቤቶችና መስክ ሥራ ክንውን መምሪያ | ✔ | ✔ | ✔ | ✕ |
| 4 | የሕትመት አገልግሎት | ✔ | ✔ | ✔ | ✕ |
| 5 | የሰው ሀብትና ሥራ አመራር መምሪያ | ✔ | ✔ | ✔ | ✕ |
| 6 | የፋይናንስ መምሪያ | ✔ | ✔ | ✕ | ✕ |
| 7 | የቴክኒክና ንብረት አስተዳደር አገልግሎት | ✔ | ✔ | ✔ | ✕ |
| 8 | የስታቲስቲክስ ሜቶዶሎጂ መምሪያ | ✔ | ✔ | ✔ | ✕ |
| 9 | የኢንዱስትሪ፣ንግድና አገልግሎቶች ስታቲስቲክስ መምሪያ | ✔ | ✔ | ✔ | ✕ |
| 10 | የቤተሰብ በጀት፣የኑሮ ሁኔታ ክትትልና የዋጋዎች ስታቲስቲክስ መምሪያ | ✔ | ✕ | ✕ | ✕ |
| 11 | የዕቅድና ፕሮግራም አገልግሎት | ✔ | ✔ | ✔ | ✕ |
| 12 | የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ጽ/ቤት | ✔ | ✔ | ✔ | ✕ |
| 13 | የኦዲትና የክዋኔ መምሪያ | ✔ | ✔ | ✔ | ✕ |
| 14 | የሕዝብ ግንኙነት፣ መረጃ ስርጭትና ትምህርት አገልግሎት | ✔ | ✔ | ✔ | ✕ |
| 15 | የሕግ አገልግሎ | ✔ | ✔ | ✔ | ✕ |
| 16 | የሰው ኃይልና ማኅበራዊ ስታቲ. መምሪያ | ✔ | ✔ | ✔ | ✕ |
| 17 | የመረጃ ማቀነባበሪያ መምሪያ | ✔ | ✔ | ✔ | ✕ |
| 18 | የሕዝብ ጉዳይና ቤቶች ስታቲ. መምሪያ | ✕ | ✕ | ✕ | ✕ |
| 19 | የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲ. መምሪያ | ✕ | ✕ | ✕ | ✕ |

ማሳሰቢያ፣ በተራ ቁጥር 6 እና 10 የተጠቀሱት በሥራ ብዛት ምክንያት፣ በተራ ቁጥር 18 እና 19 የተጠቀሱት ደግሞ ከቀድሞው የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ኮሚሽን የመጡ በመሆናቸው ምክንያት የBPR ሥራ ወደ ኋላ ቀርቷል፡፡

## 9. የማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት

- በ1998 የዕቅድ ዘመን በመ/ቤቱ የተዘጋጁ 9,365 ልዩ ልዩ የጥናት ሪፖርቶች ለመንግሥት፣ ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ለምርምር ማዕከላት በነፃ ተሠራጭተዋል:: እንዲሁም 3,120 ልዩ ልዩ የጥናት ሪፖርቶችና የስታቲስቲክስ መጽሔቶች በብር 74,833.10 ሽያጭ ተፈጽሟል:: እንዲሁም ብር 33,920 የአገልግሎት ዋጋ በማስከፈል ጥሬና የተቀነባበሩ መረጃዎች ለተጠቃሚዎች የተሸጡ ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ በጠቅላላው ከሽያጭና ከአገልግሎት ክፍያ ብር 108,753.10 ለመንግሥት ገቢ ተደርጓል::

- የመ/ቤቱ ልሳን የሆነው ልሳነ ማስኤ ቅጽ 4 ቁጥር 5 መጽሔት ቅጽ 5 ቁጥር 6 ከያንዳንዳቸው 2,000 ኮፒ፣ እንዲሁም ዜና ማስኤ ቅጽ 3 ቁጥር 1 ቅጽ 4 ቁጥር 2፣ ከእያንዳንዳቸው 1500 ኮፒ ታትሞ ለመ/ቤቱ ለተለያዩ ከመሥሪያ ቤቱ ጋር የሥራ ግንኙነት ላላቸው አካላት ተሠራጭቷል::

- የመ/ቤቱን የ1997 የዕቅድ አፈጻጸም የመ/ቤቱን የ5 ዓመት የትኩረት አቅጣጫና ድረ-ገጽ ግንባታ፣ በመ/ቤቱ የተካሄደውን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት ውጤት፣ አገር አቀፍ የቤት እንስሳት ናሙና ቆጠራን፣ የአፍሪካ ስታቲስቲክስ ቀንን አላማና በዓል አከባበር፣ የመ/ቤቱን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴና የመረጃዎችን ጠቀሜታ፣ የሁለተኛውን ዙር የሥነ ሕዝብና ጤና ጥናት /DHS/ የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት መጠናቀቅና የተገኘው ውጤት፣ ዓለም አቀፍ የንጽጽር መርሃ ግብር ለአፍሪካ ጥናትና የሦስተኛው ዙር የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን፣ 1999 የህዝብና ቤት ቆጠራ በተዘጋጁት ሰነዶች ላይ ከሚመለከታቸው ጋር የተደረገውን ውይይት፣ የ1997 ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት መጠናቀቅና የ1999 የህዝብና ቤት ቆጠራ ሙከራ ሥራ ጅማሮን እንዲሁም የህዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን የመጀመሪያ ስብሰባውን ማካሄዱንና ከአገር አቀፍ የሰው ኃይል ጥናት የተገኘውን ውጤት በተመለከተ በሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋዜጣዊ መግለጫ ተሰጥቷል:: ዜናዎቹም በሬዲዮ፣በቴሌቪዥን በጋዜጦች ሽፋን እንዲያገኙ በማድረግ ለህብረተሰቡ ግንዛቤን ለማስጨበጥ ተሞክሯል::

- የመ/ቤቱ ቤተ መጻሕፍት ለመሥሪያ ቤቱ ሠራተኛና ከውጭ ለሚመጡ ተገልጋዮችና ተጠቃሚዎች ያልተቋረጠ የንባብ፣ የመረጃ አቅርቦትና የትውስት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል::

- በ1998 የዕቅድ ዘመን ውስጥ 345 የመ/ቤቱን ሪፖርቶች በመረከብና 128 ልዩ ልዩ አዳዲስ የውጭና የአገር ውስጥ ሕትመቶችን በልውውጥና በስጦታ በማሰባሰብ ቤተ መጻሕፍቱን ለማጠናከር ጥረት ተደርጓል::

- በቤተ መጻሕፍቱ ውስጥ ለውጭ ተገልጋዮች የፎቶ ኮፒ አገልግሎት በመስጠት ብር 2,045.75 ለመንግሥት ገቢ ሊሆን ችሏል::

- የ1998 አዲስ ዓመትን ምክንያት በማድረግ 6,000 የግድግዳና 6,000 የኪስ ቀን መቁጠሪያዎች ተዘጋጅተውና ታትመው ለሚመለከታቸው መ/ቤቶችና እንዲሁም ለመ/ቤቱ ሠራተኞች ተሰጥቷል::

- በማስታወቂያ ሚኒስቴር በሚዘጋጀው ኢትዮጵያ ዓመታዊ መጽሐፍ ውስጥ የመ/ቤቱን የ1997 በጀት ዓመት እንቅስቃሴ በተመለከተ የሚወጣ ጽሑፍ ተዘጋጅቶ የተላከ ሲሆን፣ ጽሁፉም በመጽሔት ታትሞ ወጥቷል:: አዳዲሶቹን በማስኤና የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጆች ተዘጋጅተው ለቅ/ጽ/ቤቶች እንዲደርሱ ተደርገዋል:: መ/ቤቱ የሚያወጣቸውን ሪፖርቶች ይዘት የህትመት ጊዜና መሰል መረጃዎችን በሚመለከት ብሮሽር ተዘጋጅቶ ለመረጃ ተጠቃሚዎች በመሠራጨት ላይ ሲሆን የመ/ቤቱን ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ አላማና ዋና ዋና ተግባራትን አካቶ የያዘ ብሮሽር በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተዘጋጅቶ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ቀርቧል::

- መ/ቤቱ ካከናወናቸው አያሌ ተግባራት መካከል አስፈላጊ ናቸው ተብሎ የታመነባቸውን የተወሰኑ በፎቶና በቪዲዮ ተቀርጸው ለመረጃነት እንዲቀመጡ ተደርጓል:: እንዲሁም መ/ቤቱ የተካፈለበትን ኤግዚቢሽን የማደራጀት የማዘጋጀትና ለጐብኝዎችም የማስረዳት ተግባር ተከናውኗል::

## 10 የኦዲት አገልግሎት

- በ1998 የዕቅድ ዘመን የመ/ቤቱን ገንዘብ ቤትና የዕቃ ግምጃ ቤት ሐምሌ 1/1997 ዓ.ም በማሸግ የገንዘብ ቤቱ የምርምራ ሥራና እንዲሁም የዕቃ ግምጃ ቤቱ የአላቂ ንብረቶች ቆጠራ ተደርጎና ሪፖርቱ ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ተላልፏል።

- የመ/ቤቱ የየወሩ የሳጥን ወይም የካዝና ምርመራና የዕቃ ግምጃ ቤት የቋሚ ንብረት ገቢና ወጪ ምርመራ፣ እንዲሁም የመ/ቤቱ የመኪና መለዋወጫ ዕቃ ግምጃ ቤት ቆጠራ ምርመራ ተካሄዶ ሪፖርቱ ለመ/ቤቱ ለበላይ አካል ቀርቧል።

- የ1996 ዓ.ም በጀት ዓመት ሂሣብ አጠቃላይ ገቢና ወጪ ተገናዝቦ ምርመራው ተጠናቆ ሪፖርቱ ለመ/ቤቱ የበላይ አካል የቀረበ ሲሆን፣ የ1997 በጀት ዓመትም ዝርዝር ምርመራው ተጠናቆ በጀቱን ለመዝጋት የማስተካከያ ሥራውን ለማከናወን ዝግጅት እየተደረገ ሲሆን፤ የ1998 በጀት ዓመት እስከ ጥር ወር 1998 ያለው ዝርዝር የሂሣብ ምርመራም ተካሄዷል።

- የመ/ቤቱን የሩብ ዓመት ሪፖርት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ወቅቱን ጠብቆ ለማቅረብ የተቻለ ሲሆን፤ በዚህ ሪፖርት ውስጥ የመጽሐፍ ቆጠራና ምርመራ ለቅ/ጽ/ቤቶች በባንክ የተላከ ገንዘብ ዝርዝር ምርመራ የቼክ ክፍያዎች ምርመራ ተካሄዷል።

## 11. ሕግ አገልግሎት

- መ/ቤቱ ለትምህርት ወደ ውጪ አገርና በአገር ወስጥ ልኳቸው ትምህርታቸውን አጠናቀው ሲመለሱ በገቡት ግዴታ መሠረት መ/ቤቱን ባለማገልገላቸው ምክንያት ሳይሠሩ የተከፈላቸውን ደመወዝ እንዲከፍሉ በተለያዩ ፍርድ ቤቶች ክስ ከተመሠረተባቸው ግለሰቦች መካከል እስካሁን በተደረገው ክትትል ፍ/ቤቱ እንዲከፍሉ በወሰነው መሠረት ከሁለት ግለሰቦች በጠቅላላው ብር 11,457.07 ገቢ የተደረገ ሲሆን ሶስተኛው ግለሰብ ደግሞ

ከነወለዱ ብር 74,106.63 እንዲከፍል ተወስኖበት ከደመወዙ 1/3 እየተቆረጠ ለመ/ቤቱ ገቢ እንዲሆን ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

- በሌላ በኩል አንድ ግለሰብ ያጐደለውን የመንግሥት ገንዘብ ገቢ እንዲያደርግ መ/ቤቱ በመሰረተው ክስ ላይ በተደረገው ክትትል ግለሰቡ ብር 11,395.09 እንዲከፍል ፍ/ቤቱ በወሰነው መሠረት ለመ/ቤቱ ገቢ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም አንድ ሠራተኛ ያጐደሉትን ብር 67.50 እንዲከፍሉ በተጠየቁት መሰረት ገንዘቡን ገቢ አድርገዋል፡፡

- የአፍሪካ ኢንሹራንስ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቤቱ ያቀረበው የብር 5,649.98 እና አንድ ግለሰብ ያቀረቡት የብር 42,960 የይገባኛል የጉዳት ካሳ ክስ፤ እንዲሁም በሌላ በኩል ሁለት ግለሰቦች ያጐደሉትን የመንግሥት ገንዘብ እንዲከፍሉ መ/ቤቱ ባቀረበው የብር 82,082.42 ክስ ላይ ክትትል የተደረገ ሲሆን እስካሁን ጉዳዩ ዕልባት ሳያገኝ በቀጠሮ ላይ ይገኛል፡፡

- እንዲሁም ሁለት የመ/ቤቱ ሠራተኞች በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍ/ቤት በመ/ቤቱ ላይ ያቀረቡት የይገባኛል ክስ አንደኛውን የዲሲፕሊን ኮሚቴው የወሰነውን የ2 ወር ደመወዝ ቅጣት አሻሽሎ የ1 ወር ከ10 ቀን ደመወዝ እንዲቀጣ የወሰነ ሲሆን፣ የሁለተኛውን ግለሰብ ደግሞ የዲስፕሊን ኮሚቴው ውሳኔ ትክክል አይደለም በማለት ሽሮታል እንዲሁም የሶስተኛውን ግለሰብ ይግባኝ በተመለከተ የመ/ቤቱ የዲስፕሊን ኮሚቴ ጉዳዩን በድጋሚ ተመልክቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት ወስኗል፡፡

## 12. ፕላንና ፕሮግራም አገልግሎት

- በ1998 በጀት ዓመት መ/ቤቱ ለሚያካሂዳቸው ሁለት ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ ከመንግሥት የተፈቀደውን ካፒታል በጀት ከሚመለከታቸው መምሪያዎችና አገልግሎቶች ጋር በመሆን በወርሃዊ የሥራ መርሃ ግብሩ መሠረት ወርሃዊ የገንዘብ ፍላጐት አዘጋጅቶ ለሚመለከተው ክፍል እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡

- የ1998 በጀት ዓመት የስታቲስቲክስ የሥራ ዕቅድን በተፈቀደው በጀት መጠን አስተካክሎ ለመ/ቤቱ የበላይ አካልና ለሁሉም መምሪያዎችና አገልግሎቶች ለክትትል እንዲያመች አዘጋጅቷል::

- የኤጀንሲውን የመጀመሪያ ሩብ ዓመት፣ የስድስትና የዘጠኝ ወራት ሪፖርት በማጠናቀርና በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው ክፍሎች እንዲደርስ አድርጓል::

- የ1999 በጀት ዓመት የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም እና የሦስተኛ ዙር የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የካፒታል በጀት ፍላጐት የሚገልጽ የፕሮጀክት ዶክመንት ከሚመለከታቸው መምሪያዎችና አገልግሎቶች ጋር በመሆን አዘጋጅቶ ለመንግሥት አቅርቧል::

## 13. የአስተዳደርና ፋይናንስ አገልግሎት

### 13.1 የሰው ኃይል

በ1998 በጀት ዓመት መጀመሪያ ላይ በኤጀንሲው መ/ቤት 1,538 ቋሚና 2,339 የኮንትራት በጠቅላላው 3,877 ሠራተኞች ነበሩ:: በዚህ በጀት ዓመት ከቋሚ ሠራተኞች መካከል 41 በተለያዩ ምክንያት ከሥራ ተሰናብተዋል:: እንዲሁም ሁለት በጡረታ የተገለሉ ሲሆን፣ 24 በሞት ተለይተዋል:: በአንጻሩም የ67 አዲስ ሠራተኞች ቅጥር ሲፈጸም 119 ከህዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት የመጡ ሲሆን፣ አምስት ደግሞ በመንግሥት ትዕዛዝ ወደ መ/ቤቱ እንዲመለሱ ተደርጓል:: በሌላ በኩል 2,339 የኮንትራት ሠራተኞች ውስጥ 5,889 ከመ/ቤቱ ሲሰናበቱ 133 ሹፌሮች፣ 6 የጥበቃ ሠራተኞች፣ 27 የሂሳብ ሠራተኞች፣ 4,480 ጀማሪ መረጃ ሰብሳቢዎችና ረዳት ካርታ ሠራተኞች፣ 109 ዳታ ኢንትሪ ኦፕሬተሮች፣ 120 ጀማሪ ስታቲስቲሺያንና ረዳት ካርታ ተቆጣጣሪዎች 1 የጠቅላላ መካኒክ ቅጥር ተፈጽሟል::

በዚህም መሠረት በ1998 የዕቅድ ዘመን መጨረሻ ላይ ያለው ጠቅላላ የሰው ኃይል 2,988 ሲሆን ከዚህ ውስጥ 1,662 ቋሚና 1,326 የኮንትራት ሠራተኞች ናቸው::

ሠንጠረዥ 3 <u>የሰው ኃይል ሁኔታ</u>

| ተ ቁ | አጠቃላይ ሁኔታ | የሠራተኛ ቅጥር ሁኔታ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ቋሚ | ኮንትራት | ድምር |
| 1 | በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የነበሩ | 1,538 | 2,339 | 3,877 |
| 2 | አዲስ የተቀጠሩ | 67 | 4,876 | 4,943 |
| 3 | በመንግሥት ትዕዛዝ ወደ ሥራ የተመለሱ | 5 | - | 5 |
| 4 | ከህዝብና ቤት ቆጠራ፣ ዝውውር ወደ መ/ቤቱ የመጡ | 119 | - | 119 |
| 5 | በተለያዩ ምክንያት ሥራ የለቀቁ | (41) | (5,889) | (5,930) |
| 6 | በጡረታ የተለዩ | (2) | - | (2) |
| 7 | በሞት የተለዩ | (24) | - | (24) |
| 8 | አሁን በሥራ ላይ ያሉ | 1,662 | 1,326 | 2,988 |

ከዚህ በታች በሠንጠረዥ የተገለፀው የሰው ኃይል በአገልግሎት ዓይነት ሲተነተን ቋሚ ሠራተኞችን በሚመለከት 201 በፕሮፌሽናል፣ 808 መለስተኛ ፕሮፌሽናል፣ ሲሆን 653 የአስተዳደርና የጽሕፈትና የጠቅላላ አገልግሎት ሠራተኞች ናቸው::

## 13.2 <u>የበጀት አጠቃቀም</u>

ለ1998 በጀት ዓመት የኤጀንሲው መ/ቤት ከመንግሥት የተፈቀደለት የመደበኛ እና የካፒታል በጀት በጠቅላላው ብር 82,414,200 ነው:: ከዚህ ውስጥ ብር 36,636,700 ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ፣ ብር 28,120,000 ለሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ፕሮጀክት ለካርታ ሥራ የቅድመ ዝግጅት የሚውል ሲሆን ብር 17,657,500 ለመደበኛ ሥራ ማስኬጃና ለደመወዝ ክፍያ የሚውል ነው:: እንዲሁም በተጨማሪ በጀት ለሕዝብና ቤት ቆጠራ ብር 13,750,000 ተፈቅዷል::

### 13.2.1 የመደበኛ በጀት አጠቃቀም

ለበጀት ዓመቱ ከተመደበው ብር 17,657,500 ውስጥ በዕቅድ ዘመኑ ማለትም ከሐምሌ 1/97 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/98 ዓ.ም ድረስ ብር 17,657,500 ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተጠይቆ ገቢ የተደረገ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ ብር 16,936,285 ሥራ ላይ ውሏል:: ሥራ ላይ ከዋለው ብር ውስጥ 15,217,777 (90%) ያህሉ ለደመወዝ የተከፈለ ሲሆን፤ ብር 1,718,509 (10%) ደግሞ ለሥራ ማስኬጃ የዋለ ነው:: በጠቅላላው ሥራ ላይ የዋለው ገንዘብ ለመ/ቤቱ ከተፈቀደው ጋር ሲነፃፀር 96% ያህሉን እንደሆነ ያመለክታል::

**የመደበኛ በጀት አጠቃቀም**

**ሠንጠረዥ 4**

| የወጪ ርዕስ | ለዓመቱ የተመደበ በጀት | በበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው ውስጥ ተጠይቆ የመጣ | ተጠይቆ ገቢ ከሆነው ውስጥ ሥራ ላይ የዋለ | አፈጻጸም በመቶኛ ከዓመቱ |
|---|---|---|---|---|
| 01 | 02 | 03 | 04 | 05 |
| ደመወዝ | 15,278,449 | 15,278,449 | 15,217,777 | 99.6 |
| ሥራ ማስኬጃ | 2,379,051 | 2,379,051 | 1,718,509 | 72 |
| ድምር | 17,657,500 | 17,657,500 | 16,936,286 | 96 |

### 13.2.2 የካፒታል በጀት አጠቃቀም

በ1998 በጀት ዓመት ኤጀንሲው ለሚያካሄዳቸው ሁለት ፕሮጀክቶች በጠቅላላው ብር 82,414,200 ተፈቅዶለታል:: ከዚህ ውስጥ ብር 36,636,700 ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ማስፈጸሚያና ብር 28,120,000 ደግሞ በ1999 ዓ.ም ለሚካሄደው የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ የቅድመ ዝግጅት ለካርታ ሥራ የሚውል ነው::

በዚህም መሠረት የሁለቱን ፕሮጀክቶች የበጀት አጠቃቀም በተነናጠል እንደሚከተለው ለማመልከት ተሞክሯል::

## ሀ. ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም

በ1998 በጀት ዓመት ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የተፈቀደው ብር 36,636,700 ሲሆን፤ በዕቅድ ዘመኑ ማለትም ከሐምሌ 1/1997 እስከ ሰኔ 30/1998 ድረስ 36,636,700 ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተጠይቆ ገቢ ሆኖ ብር 32,601,660 ሥራ ላይ ውሏል፡፡ ሥራ ላይ የዋለው ገንዘብ ለመ/ቤቱ ከተመደበው ጋር ሲነፃፀር አፈፃፀሙ 89% እንደሆነ ያመለክታል፡፡

### የብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም በጀት አጠቃቀም

ሠንጠረዥ 5

| የሂሣብ መደብ | ለ1998 በጀት ዓመት የተፈቀደ | ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው ውስጥ ከገ/ኢ/ል ሚኒስቴር ተጠይቆ ገቢ የሆነ | ገቢ ከሆነው ውስጥ ሥራ ላይ የዋለው | አፈጻጸም በመቶኛ ከዓመቱ |
|---|---|---|---|---|
| 6113 | 12,765,890 | 12,765,890 | 12,404,406 | 97 |
| 6114 | 2,627,700 | 2,627,700 | 1,347,972 | 51 |
| 6123 | 880,900 | 880,900 | 949,432 | 108 |
| 6211 | 366,200 | 366,200 | 245,445 | 67 |
| 6212 | 300,000 | 300,000 | 164,924 | 55 |
| 6213 | 350,000 | 350,000 | 169,797 | 49 |
| 6217 | 3,254,000 | 3,254,900 | 2,104,007 | 65 |
| 6231 | 9,281,620 | 9,281,620 | 8,846,091 | 95 |
| 6232 | 871,590 | 871,590 | 926,121 | 106 |
| 6241 | 3,547,000 | 3,547,000 | 3,421,862 | 96 |
| 6243 | 60,000 | 60,000 | 8,838 | 15 |
| 6252 | 642,700 | 642,700 | 565,624 | 88 |
| 6254 | 1,090,100 | 1,090,100 | 1,090,100 | 100 |
| 6255 | 30,000 | 30,000 | 10,780 | 36 |
| 6257 | 40,000 | 40,000 | 36,048 | 90 |
| 6258 | 340,000 | 340,000 | 140,773 | 41 |
| 6259 | 64,000 | 64,000 | 77,263 | 120 |
| 6271 | 125,000 | 125,000 | 92,177 | 74 |
| ድምር | 36,636,700 | 36,636,700 | 32,601,660 | 89 |

ለ. <u>ለቆጠራ ካርታ ሥራ ፕሮግራም</u>

በ1999 ለሚካሄደው የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ፕሮጀክት ለቆጠራ ቦታ ካርታ ዝግጅት በ1998 በጀት ዓመት ብር 28,120,000 ከመንግሥት የተፈቀደውና በተጨማሪ በጀት ለተሽከርካሪ ግዥ ብር 13,750,000 ሲሆን፣ በዕቅድ ዘመኑ ውስጥ ብር 41,870,000 ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተጠይቆ ገቢ ሆኖ ብር 32,855,602 ሥራ ላይ ውሏል። ጥቅም ላይ የዋለው ገንዘብ ለዓመቱ ከተፈቀደው ጋር ሲነፃፀር 78 ከመቶው ያህሉን ነው።

<u>የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ ፕሮግራም በጀት አጠቃቀም</u>

ሠንጠረዥ 5

| የሂሣብ መደብ | ለ1998 በጀት ዓመት የተፈቀደ | ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው ውስጥ ከገ/ኢ/ል ሚኒስቴር ተጠይቆ ገቢ የሆነ | ገቢ ከሆነው ውስጥ ሥራ ላይ የዋለው | አፈጻጸም በመቶኛ ከዓመቱ |
|---|---|---|---|---|
| **6113** | **5,777,200** | **5,777,200** | **4,446,358** | **77** |
| **6114** | **1,637,600** | **1,637,600** | **1,192,157** | **73** |
| **6123** | **315,000** | **315,000** | **206,582** | **66** |
| **6212** | **3,700,000** | **3,700,000** | **1494576** | **40** |
| **6213** | **100,000** | **100,000** | **25,443** | **25** |
| **6217** | **3,400,000** | **3,400,000** | **1,774,864** | **52** |
| **6231** | **9,500,000** | **9,500,000** | **10,110,742** | **106** |
| **6232** | **338,000** | **338,000** | **225,715** | **67** |
| **6241** | **2,300,000** | **2,300,000** | **2,346,134** | **102** |
| **6243** | **180,000** | **180,000** | **30,750** | **17** |
| **6254** | **177,400** | **177,400** | **216,848** | **122** |
| **6255** | **20,000** | **20,000** | **14,980** | **75** |
| **6258** | **130,000** | **130,000** | **108,412** | **83** |
| **6259** | **90,000** | **90,000** | **76,052** | **84** |
| **6271** | **450,000** | **450,000** | **235,322** | **52** |
| **6311** | 13,750,000* | 13,750,000* | 10,350,667 | 75 |
| **6314** | **4,800** | **4,800** | **-** | **-** |
| **ድምር** | **41,870,000** | **41,870,000** | **32,855,602** | **78** |

* ለተሽከርካሪ ግዥ ብር 13,750,000 በተጨማሪ በጀት መፈቀዱ ይታወቃል። እንዲሁም ብር 17,089,388 ደግሞ ተገዝተው ለመጡት ተሽከርካሪዎች የታክስ ክፍያ በገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር በኩል ተከፍሏል።

### 13.3 አገልግሎት ነክ የሆኑ ሥራዎች

#### 13.3.1 ጠቅላላ አገልግሎት ዋና ክፍል

- በ1998 በጀት ዓመት በዋናው መ/ቤትና በስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶች የደንብ ልብስ የሚያስፈልጋቸውን የሠራተኛ ቁጥር በማጣራት የስም ዝርዝራቸው እንዲሰበሰብ ተደርጐ ጨረታ በጋዜጣ ወጥቶ አሸናፊው በጨረታ ኮሚቴ ተለይቶ ከአሸናፊው ድርጅት የደንብ ልብሱ ተገዝቶ ለሚመለከታቸው ሠራተኞች ተሠራጭቷል።

- በዕርዳታ የተላኩ 16 ፕሪንተሮች፣ 25 ኮምፒውተሮች፣ 26 የፎቶ ኮፒ ማሽኖች ገቢ ተደርገዋል። የዋናው መ/ቤት የንብረት ቆጠራ ተደርጐ ሪፖርቱ ቀርቧል።

- የአንድ ዓመት የኮምፒውተር ፕሪንተር የጥገና ኮንትራት በግልጽ ጨረታ በጋዜጣ እንዲወጣ ተደርጐ አሸናፊውን የመለየት ሥራ በጨረታ ኮሚቴው ተከናውኖ ከአሸናፊው ጋር ውለታ ተፈጽሞ የጥገና ሥራው በመካሄድ ላይ ይገኛል።

- የመ/ቤቱን የጽ/መሣሪያ የህትመት አላቂ ዕቃዎች ቋሚ ዕቃዎችና የካርቶግራፊ ዕቃዎችንና የመኪና ጐማዎችን ግዥ ለመፈጸም በግልጽ ጨረታ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ወጥቶ ተጫራቾች ከተሳተፉ በኋላ በጨረታ ኮሚቴው አሸናፊው ተለይቶ ከአሸናፊው ጋር ውለታ በመዋዋል ግዥው ተፈጽሟል።

- መ/ቤቱ የተጠቀመባቸውን የስልክ፣ የመብራት፣ የውሃ ፍጆታና የኢንተርኔት ክፍያዎችን በሚመለከት አስፈላጊውን መረጃ ቢሉን በማየት የብር 484,764 ክፍያ እንዲፈጸም ተደርጓል። እንዲሁም ለመጋዘንና ለተለያዩ አገልግሎት ለዋሉ የቤት ኪራይ ብር 657,586.56 ክፍያ ተፈጽሟል።

- በመ/ቤቱ የሚገኙትን የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች መ/ቤቱ ሊጠቀምባቸው የሚችሉትንና የማይጠቀምባቸውን በመለየት በንብረት አወጋገድ መመሪያ መሠረት እንዲከናወን ለማድረግ ለሚመለከተው አካል

በማሳሰቢያ ተጠይቆ ምላሹ ስለተገኘ ሥራውን ለማከናወን ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ ነው።

- የመ/ቤቱ ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ተካሂዶ ለተተኪ ዕቃ ግምጃ ቤት ሠራተኛ በአረካካቢ ኮሚቴ አማካይነት ርክክብ ተፈጽሟል።

- በመ/ቤቱ ለረጅም ጊዜ አገልግሎት በሰጡና በአሁኑ ሰዓት ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ ልዩ ልዩ የመረጃ ወረቀቶችን በንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ አማካኝነት በተወሰነው መሠረት እንዲወገድ የተደረገ ሲሆን፤ እንዲሁም አሮጌ ጐማዎችና የመኪና ባትሪዎች በመንግሥት ደንብ መሠረት የማስወገድ ሥራ ተካሄዷል።

- የመ/ቤቱን የቢሮ ጥበት ለማቃለል የአስተዳደርና ፋይናንስ አገልግሎት የሚጠቀምበትን ህንጻ በመከፋፈል የተወሰኑ ሠራተኞችን ለማስተናገድ ጨረታ ወጥቶ አሸናፊውም ተለይቶና ሥራው ተጠናቆ የውስጥ ድርጅቱን በማሟላት ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል።

- የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች የሚጠቀሙበት የጐማ ግዥ ለመፈጸም ጨረታ በጋዜጣ ወጥቶ ግዥው ተፈጽሟል። እንዲሁም የመ/ቤቱ የኤሌክትሪክ አውቶማቲክ ስዊች ችግር ስለነበረበት በመብራት ኃይል በኩል እንዲቀየር የተደረገ ሲሆን የእስቶክ ካርድ ምዝገባዎች ተከናውነዋል።

- መ/ቤቱ ባለው አነስተኛ ጋራዥ ውስጥ ያለውን የመሥሪያ ቦታ ጥበት ችግር ለመቅረፍ አንድ አነስተኛ የሥራ ቦታ /የሽራ መጠለያ/ ተዘጋጅቶ ለሥራ ብቁ እንዲሆን ተደርጓል።

### 13.3.2 <u>ትራንስፖርትና ጥገና ክፍል</u>

- የመ/ቤቱ 132 ተሽከርካሪዎች በዋናው መ/ቤት ጋራዥ የጥገና ሥራ ተካሄዶ ወደ ሥራ ተሰማርተዋል። እንዲሁም 37 ተሽከርካሪዎች በኢንሹራንስ ተጠግነው ለሥራ ብቁ የሆኑ ሲሆን 5 ተሽከርካሪዎች በጥገና ላይ ይገኛሉ። የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች በአብዛኛው ዓመታዊ የደህንነት ምርመራ ተደርጐላቸው ወደ ምድብ ቦታቸው ተሰማርተዋል።

- በጨረታ ኮሚቴ የተመረጡ የ6 ጋራዦች ውል ተፈጽሟል:: እንዲሁም የ248 ተሽከርካሪዎች የኢንሹራንስ አገልግሎት እንዲያገኙ ከመድን ጋር የውል ዕድሳት የተፈጸመ ሲሆን 21 ተሽከርካሪዎች በመድን ድርጅት ጥገናና ዕድሳት ተደርጐላቸው ለስምሪት ብቁ ሆነዋል::

- 24,518 ሊትር ቤንዚን፣ 17,300 ሊትር ናፍታ፣ እንዲሁም ለሞተር ለመሪና፣ ለጥርሳጥርስ የሚውል 833 ሊትር ዘይትና 20 ኪሎ ግሪስ ተሽከርካሪዎች እንዲያገኙ ተደርጓል::

- መ/ቤቱ ለገዛቸው 50 ቶዮታ ላንድ ክሩዘር መኪናዎች አዲስ የፊትና የኋላ ሠሌዳ እንዲለጠፍ ተደርጓል:: ለዚህም ተግባር ብር 17,000 ወጪ ሆኗል::

- 406 ተሽከርካሪዎችም በተለያዩ የደንበኞች ጋራዦች ጥገና ተደርጐላቸዋል:: እንዲሁም 44 ተሽከርካሪዎች በጥገና ላይ ይገኛሉ፣ ይህም አንድ መኪና በዓመት ሁለትና ሶስት ጊዜ ጥገና ስለሚከናወንለት ነው::

- ለ25ቱም የስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶች ስለተሽከርካሪዎች አያያዝና አጠቃቀምን በሚመለከት መመሪያ ተዘጋጅቶ ተሠራጭቷል፣ የተሽከርካሪ የጥገና ሂደታቸውም ምርመራ በማካሄድ ተረጋግጧል::

### 13.3.3 ሕትመት ዋና ክፍል

በበጀት ዓመቱ ውስጥ በጠቅላላው 173,581 ጥራዝ ባለ 13,742,423 ገጾች የተለያዩ የሕትመት ሥራዎች ለመ/ቤቱ የተለያዩ የሥራ ክፍሎች አገልግሎት ሰጥቷል::

## 14. የዕቅድ አፈፃፀሙ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች

እያደገ የመጣውን የመረጃ ፍላጐት ለማሟላት እንዲቻል በየወቅቱ ቁጥራቸው በዛ ያለ ባለሙያዎች የሚቀጠር ሲሆን፣ ከዚህ በፊትም የተቀጠሩት ለሥራቸው ምቹ የሆነ ቢሮ ለማግኘት ከመ/ቤቱ አቅም በላይ እየሆነ መጥቷል፡፡ በተለይም ደግሞ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽንን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 449/97 መሠረት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲን የኮሚሽኑ ጽ/ቤት እንዲሆን የደነገገ ሲሆን፣ በጽ/ቤቱ የሚሠሩ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን ተረክቦ በማሰራት ላይ ነው፡፡ ሆኖም በአንድ አካባቢ አድረጐ ለማሠራት በቂ የሥራ ቦታ ባለመገኘቱ በሁለት ቦታዎች ሆነው ሥራቸውን እንዲሠሩ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ይህ ደግሞ በአጠቃላይ የኤጀንሲው ሥራ ላይ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡

ይህም በመሆኑ በርካታ የሥራ ኃላፊዎችና ኤክስፐርቶቻቸው ተራርቀው የሚሠሩበት እንዲሁም አንድ ክፍል ከአቅም በላይ የሆነ የሰው ብዛት እንዲይዝ በማድረጋችን ቢሮዎቻችን ለሠራተኞች የተመቹ የሥራ ቦታ ሊሆኑ ባለመቻላቸው የሠራተኞች የሥራ ተነሣሽነት እየቀነሰ የሚመጣበት ሁኔታን እየፈጠረ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም ከፍተኛ የመንግሥት ሀብት የወጣባቸው የተለያዩ የመስክ መገልገያ ዕቃዎች በተለያዩ ጊዜያት መረጃ የተሰበሰበባቸው የጥናት ዶክመንቶችና ሌሎች ቁሣቁሶች አመች የሆነ ማከማቻ መጋዘን ባለማግኘታቸው ችግሩን የተደራረበ አድርጐታል፡፡ እንዲሁም በመላው አገሪቱ የተከፈቱ የስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶች ላይ ተመሣሣይ የሆነ የቢሮና የመጋዘን ችግር ያለባቸው ሲሆን፣ በዓመት መንግሥት ለዋና መ/ቤትና ለቅ/ጽ/ቤቶቹ ከግማሽ ሚሊዮን ብር በላይ ለኪራይ ወጪ ያደርጋል፡፡ በመሆኑም ለዋናው መ/ቤትና ለቅ/ጽ/ቤቶቻችን ለሥራ አመቺ የሆነ ቢሮ ለማግኘት እንድንችል ህንፃዎቹ የሚገኙበት መንገድ እንዲመቻች እንጠይቃለን፡፡